የኢትዮጵያ
ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN
RIGHTS COMMISSION

በኢትዮጵያ ሰብአዊ
መብቶች ኮሚሽን የተዘጋጀ

# በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ የጥቃት ተጎጂ የሆኑ ሴቶች እና ሕፃናት ሰብአዊ መብቶች አያያዝን የተመለከተ የክትትል ሪፖርት



Phot o Credit: Israel Solomon, Media and Communications Department, EHRC

## መጋቢት 2016 ዓ.ም.

www.ehrc.org

## ማውጫ

**ክፍል አንድ ........ 4**

**መግቢያ ........ 4**

1.1 ዳራ ........ 4

1.2 የክትትሉ ዓላማ........ 5

1.3 የክትትሉ ወሰን ........ 5

1.4 የክትትሉ አስፈላጊነት........ 6

1.5 የክትትሉ ሥነ-ዘዴ ........ 7

1.6 የክትትሉ ውስንነቶች ........ 9

**ክፍል ሁለት ........ 10**

**አግባብነት ያላቸው የሕግ እና የፖሊሲ ማዕቀፎች ........ 10**

2.1 የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ያላቸው መብቶች በዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች እና ሰነዶች ........ 10

2.1.1 ፍትሕ የማግኘት መብት ........ 11

2.1.2 ክብርን በጠበቀ እና ለሁለተኛ ደረጃ ጥቃት በማያጋልጥ መልኩ የመስተናገድ መብት .. 12

2.1.3 ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ የፍትሕ አገልግሎት የማግኘት መብት........ 14

2.1.4 የደኅንነት ጥበቃ የማግኘት መብት ........ 14

2.1.5 የመሰማት /የመሳተፍ መብት ........ 15

2.1.6 የተፋጠነ ፍትሕ እና ውጤታማ መፍትሔ የማግኘት መብት ........ 17

2.1.7 የድጋፍ አገልግሎት የማግኘት መብት ........ 19

2.2 የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ያላቸው መብቶች በኢትዮጵያ የሕግ ማዕቀፍ........ 19

2.2.1 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢ.ፌ.ዴ.ሪ.) ሕገ-መንግሥት ........ 19

2.2.2 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ........ 20

2.2.3 የኢትዮጵያ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ........ 21

**ክፍል ሦስት ........ 23**

**ዋና ዋና ግኝቶች ........ 23**

3.1 ፍትሕ የማግኘት መብት ........ 23

3.2 ክብርን በጠበቀ እና ለዳግም ጥቃት በማያጋልጥ መልኩ የመስተናገድ መብት ........ 27

3.3 ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ የፍትሕ አገልግሎት የማግኘት መብት........ 28

3.4 የደኅንነት ጥበቃ የማግኘት መብት ........ 29

3.5 የመሰማት /የመሳተፍ መብት ........ 30

3.6 የተፋጠነ ፍትሕ እና ውጤታማ መፍትሔ የማግኘት መብት........ 30

3.7 የድጋፍ አገልግሎት የማግኘት መብት ........ 32

3.8 በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ የጥቃት ተጎጂ የሆኑ ሴቶችና ሕፃናት መብት ጥሰት ምክንያቶች ........ 32

**ክፍል አራት ........ 34**

**ማጠቃለያ እና ምክረ ሐሳቦች ........ 34**

4.1 ማጠቃለያ ........ 34

4.2 ምክረ-ሐሳቦች ........ 34

## ምሕጻረ- ቃላት

| | |
|---|---|
| CEDAW | Convention on the Elimination of All forms of Discrimination against Women |
| **ኢ.ፌ.ዴ.ሪ.** | የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ |
| **ወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ** | የወንጀል መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ |
| **ዓ.ም.** | ዓመተ ምህረት |
| **ጽ/ቤት** | ጽሕፈት ቤት |
| **ፍ/ቤት** | ፍርድ ቤት |

## አንኳር ጉዳዮች

የጥቃት ተጎጂ ሴቶች እና ሕፃናት በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ውስጥ ከአቤቱታ አቀራረብ ሥርዓት ጀምሮ በምርመራ ሂደት፣ በክስ አቀራረብና አሰማም፣ እንዲሁም በድኅረ ችሎት በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ማዕቀፎች የተጠበቁላቸው መብቶች አሏቸው፡፡ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ምላሽ አሰጣጥ የተጎጂዎችን ሰብአዊ መብቶች ማእከል ያደረገ መሆን የጥቃት አድራሹን ተጠያቂነት እና የተጎጂዎችን ፍትሕ የማግኘት መብት እንዲረጋገጥ ከማድረጉም በላይ፣ የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት በፍትሕ ሥርዓቱ የሚኖራቸውን እምነት በማሳደግ ረገድ የጎላ ሚና ይኖረዋል፡፡ መንግሥትም እነዚህን መብቶች ተፈጻሚ ለማድረግ የሴቶችና ሕፃናትን ተጋላጭነት እና ብዝኀነት ታሳቢ ያደረጉ እርምጃዎችን በመውሰድ፤ በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ የጥቃት ተጎጂ ሴቶች እና ሕፃናት መብቶች አያያዝ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መርሖችን ባከበረ መልኩ እንዲሆን የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ/ኮሚሽኑ) በአዋጅ በተሰጠው የሰብአዊ መብቶችን አፈጻጸም የመከታተል ኃላፊነት መሠረት ከሚያዚያ 30 ቀን 2015 ዓ.ም. እስከ ግንቦት 4 ቀን 2015 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ በሰባት ክፍለ ከተሞች (አቃቂ ፣ አራዳ፣ ቦሌ፣ ንፋስ ስልክ፣ ልደታ፣ ቂርቆስ እና ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማዎች) እና በኦሮሚያ ክልል በሸገር ከተማ አስተዳደር፣ በቡራዩ እና ሰበታ ክፍለ ከተማዎች፣ እንዲሁም ከሐምሌ 29 እስከ ነሐሴ 8 ቀን 2015 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን፣ ጅማ ከተማ እና በሸቤ ሶምቦ ወረዳ፣ በሐረሪ ክልል፣ በሐረር ከተማ እና በኤረር ወረዳ በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር የጥቃት ተጎጂ ሴቶች እና ሕፃናት ሰብአዊ መብቶች አያያዝ ላይ ክትትል አከናውኗል፡፡

በክትትሉም ከፍትሕ ተቋማት፣ ከተቀናጀ የአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ማእከላት፣ ከመጠለያ አገልግሎት መስጫ ተቋማት እና በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ሂደት ካለፉ የጥቃት ተጎጂ ሴቶች እና ሕፃናት መረጃዎች ተሰብስቧል፡፡ በተጨማሪም የክትትሉን ግኝቶች ባለድርሻ አካላት በተገኙበት የምክክር መድረክ ላይ በማቅረብ ተጨማሪ ግብአቶች በሪፖርቱ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

የክትትሉ ዓላማ በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ውስጥ የጥቃት ተጎጂ የሆኑ ሴቶች እና ሕፃናት ሰብአዊ መብቶች አያያዝን ከዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊ እና ሀገር አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መመዘኛዎች አንጻር መቃኘት ነው፡፡ በዚህ አግባብ ተጎጂዎች የተፈጸመባቸውን ወንጀል ከማመልከት ጀምሮ በጠቅላላው የወንጀል ፍትሕ ሂደት የሚያልፉባቸውን ሁኔታዎች ለመለየት፣ በምላሽ አሰጣጥ ሥርዓቱ ውስጥ የሚታዩ የመብቶች ጥሰቶችን ከነመነሻ ምክንያቶቻቸው ለመለየት እና ተገቢ ምክረ ሐሳቦችን በማቅረብ በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት ሰብአዊ መብቶች አያያዝን ለማሻሻል ያለመ ነው፡፡ ለዚህ ዓላማ የጥቃት ተጎጂ ሴቶች እና ሕፃናት በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ውስጥ ያላቸውን መብቶች የሚመለከቱ የተለያዩ ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ ስምምነቶችና ሰነዶች በሪፖርቱ ተዳሰዋል፡፡

እነዚህ ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ ስምምነቶችና ሰነዶች የጥቃት ተጎጂ የሆኑ ሴቶች እና ሕፃናት ተደራሽ የሆነ ፍትሕ የማግኘት፣ ክብርን በጠበቀ እና ምስጢራዊነቱ በተጠበቀ የፍትሕ ሥርዓት

የመስተናገድ፣ ከሁለተኛ ደረጃ ጥቃት (secondary victimization) የመጠበቅ፣ የተፋጠነ ፍትሕ እና ውጤታማ መፍትሔ የማግኘት፣ የመሰማት እና የደኅንነት ጥበቃና ድጋፍ የማግኘት መብቶች እንዳሏቸው ይደነግጋሉ። መንግሥትም እነዚህን ሰብአዊ መብቶች የማክበር፣ የማስጠበቅ እና የማሟላት ተነፃፃሪ ግዴታ አለበት።

ኢሰመኮ ክትትል ባደረገባቸው ቦታዎች የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ በሚያልፉበት ጊዜ ከላይ ከተዘረዘሩት መብቶች አብዛኞቹ ተግባራዊ እንደማይሆኑ ለማወቅ ችሏል። ለዚህም ምክንያቶቹ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕጉ የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕጻናትን አስመልክቶ ከመደበኛው የወንጀል ሥነ ሥርዓት የተለየ የሥነ ሥርዓት ሕግ አለማስቀመጡ፤ ይህንን ክፍተት ለመሙላት ከመደበኛው የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ውጪ ተጎጂ የሆኑ ሴቶችና ሕፃናት ሰብአዊ መብቶች አያያዝን የተመለከተ አስገዳጅና ወጥ ሀገር አቀፍ የሥነ ሥርዓት መመሪያ/ፕሮቶኮል አለመኖሩ፤ የጥቃት ተጎጂ ለሆኑ ሴቶችና ሕፃናት የማገገሚያ፣ የመጠለያ፣ እንደ ሕክምና እና የሥነ ልቦና አገልግሎትን ለማግኘት የሚያስችሉ መፍትሔዎች በሕግ አለመደንገጉ እንዲሁም የተቀናጀ የአንድ ማእከል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በተቀመጠላቸው የአሠራር ሥርዓት ማኑዋል መሠረት አለመሥራታቸውን የሚጨምሩ ናቸው።

## ምክረ ሐሳቦች

በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት ሰብአዊ መብቶች አያያዝ ለማሻሻል የሚከተሉት የመፍትሔ ሐሳቦች ታሳቢ ሊሆኑ ይገባል።

- በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሰነዶች ዕውቅና የተሰጣቸው የጥቃት ተጎጂዎች መብቶች በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲም ዕውቅና የተሰጣቸው በመሆኑ የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናትን የተለየ አያያዝ የሚመለከት ግልጽ የሕግ ማዕቀፍ እንዲደነገግና፤የፍትሕ ሚኒስቴርም የሕጎቹን ተግባራዊነት እንዲያስተባብር፣ እንዲከታተል እና እንዲያረጋግጥ፤
- የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር፣ የፍትሕ ሚኒስቴር፣ የክልል ፍትሕ ቢሮዎች፣ የፌዴራል እና የክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች፣ የፌዴራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች ለፍትሕ እና የድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች የጥቃት ተጎጂ ሴቶችን እና ሕፃናትን ለማስተናገድ የሚያስችል አስፈላጊውን ስልጠና የወሰዱ ሰራተኞችን እንዲያዘጋጁ እና ለዚሁ አገልግሎት ብቁ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሥርዓት እንዲዘረጉ፤
- የፍትሕ ሚኒስቴር፣ የክልል ፍትሕ ቢሮዎች፣ የፌዴራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች እንዲሁም የፌዴራል እና የክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች በአግባቡ በመቀናጀት የወንጀል ምርመራ የሚጠናቀቅበትን እና በጉዳዩ ላይ ክስ ማቅረብ የሚቻልበትን የጊዜ ገደብ በተመለከተ አስፈላጊውን መመሪያዎችን እንዲያወጡ እና ፍትሕ ሚኒስቴር ተግባራዊነቱን እንዲከታተል፤
- የፌዴራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች በወንጀል ድርጊት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ለደረሰው ጉዳት በፍርድ ቤት ወይም በሌሎች አማራጭ ዘዴዎች የካሳ ጥያቄ በማቅረብ

ተገቢውን ካሳ በአፋጣኝ እንዲያገኙ ማድረግ የሚያስችሉ አመቺ የአሠራር ሥርዓቶችን እንዲዘረጉ፤

- ፍትሕ ሚኒስቴር እና የፌዴራል ፖሊስ፣ ከክልል ፍትሕ ቢሮዎች እና ከሌሎች ባለ ድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት በወንጀል ፍትሕ አስተዳዳር በሚያልፉበት ጊዜ አስፈላጊ መረጃዎችን የሚሰጡ የመረጃ አገልግሎት ማእከላትን እንዲያቋቁሙ፤
- የፍትሕ ሚኒስቴር፣ የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የጤና ሚኒስቴር፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ አዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን እንዲሁም በክልል የሚገኙ አቻ ተቋማት የተቀናጀ የአንድ ማዕከላትን ኢኮኖሚያዊ ተደራሽነት ችግር ለመቅረፍ በቅርበት በሚገኙ ጤና ጣቢያዎች የሕግ እና የሥነ ልቦና ባለሙያዎችን ጨምሮ አስፈላጊውን የሰው ኃይል በመመደብ የአንድ ማእከል አገልግሎት እንዲሰጡ እንዲያደርጉ፤
- በተቀናጀ የአንድ ማእከል አገልግሎት የአሠራር ማኑዋል መሠረት የፍትሕ ሚኒስቴር እና የክልል ፍትሕ ቢሮዎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በተቀናጀ የአንድ ማዕከል ተቋማት የዐቃቤ ሕግ እና ፖሊስ የሥራ ክፍሎች በአካል አገልግሎት እንዲጀምሩ እንዲያደርጉ፤
- የጥቃት ተጎጂ ለሆኑ ሴቶችና ሕፃናት አስፈላጊ የሆኑ የመጠለያ፣ የማገገሚያ እንደ ሕክምና እና የሥነ ልቦና አገልግሎቶች ያሉ መፍትሔዎች በሕግ ዕውቅና እንዲሰጥ፤
- በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረት የየፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንቶች የጾታ ጥቃት የተፈጸመባቸው ሴቶች፣ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያንን አስመልክቶ በፍርድ ቤቶች የሚከፈቱ መዝገቦች በተፋጠነ ፍትሕ አገልግሎት እልባት እንዲያገኙ እና የሕግ ባለሙያ ድጋፍ እንዲሰጣቸው ለማድረግ የሚያግዙ ዝርዝር መመሪያዎችን እንዲያወጡና እንዲያስፈጽሙ፤
- የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከክልል የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ጋር በመተባበር በፌዴራል እና በክልሎች የማገገሚያ አገልግሎቶችን የሚሰጡ የመጠለያ ተቋማትን እንዲያቋቁሙ እና እንዲያስፋፉ፤
- ሕግ አውጪው የጥቃት ተጎጂዎች ሴቶች እና ሕፃናት ደኅንነት ለመጠበቅ የሚያስችል ሕግ እንዲያወጣ እንዲሁም የፍትሕ ሚኒስቴር ሕጉን ማስፈጸም የሚያስችል የአሠራር መዋቅር እንዲዘረጋ።

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

### 1.1 ዳራ

ሴቶች እና ሕፃናት ከሌሎች የማኅበረሰብ ክፍሎች በተለየ ሁኔታ ለአካላዊ፣ ጾታዊ እና ሥነ ልቦናዊ ጥቃቶች ተጋላጭ ናቸው:: ጾታን መሠረት አድርጎ የሚፈጸም ጥቃት በታሪክ በነበረ ያልተመጣጠነ የጾታ ግንኙነት፣ እንዲሁም ሴቶች የበታች እንዲሆኑ ጫና በሚፈጥሩ ማኅበራዊ ግንኙነቶች ምክንያት በሴቶች ላይ ከሚፈጸሙ አድሎአዊ ድርጊቶች አንዱ ነው:: በሴቶች ላይ የሚደረግ አድሎአዊ ልዩነት በአካልና በአእምሮ ላይ ጉዳትን የሚያስከትሉ ጾታዊ እና ወሲባዊ ጥቃቶችን፣ እንዲሁም ሕጋዊ ያልሆኑ የነጻነት ገደቦችን የሚያጠቃልል ሲሆን በአደባባይም ሆነ በግል ሕይወት የሚከሰቱ ድርጊቶችን መፈጸም ወይም ለመፈጸም ማስፈራራትን፣ የማስገደድ ወይም ከሕግ ውጪ ነጻነትን የማሳጣት ሁኔታን ያጠቃልላል::[1]

እነዚህ ጥቃቶች በየትኛውም አጋጣሚ በማንኛውም ሰው ሊፈጸሙ ይችላሉ:: በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች በተጎጂዎቹ ላይ ከሚያደርሱት አካላዊ እና ሥነልቦናዊ ጉዳቶች በተጨማሪ በሴቶች ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አላቸው:: በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች፣ በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውንም አድሎአዊ ልዩነት ለማስወገድ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነትን ጨምሮ በተለያዩ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች እና ድንጋጌዎች ዕውቅና ያገኙ ሰብአዊ መብቶቻቸውን በአግባቡ/በተሟላ ሁኔታ እንዳይጠቀሙ የሚያደርጉም ናቸው::

ሕፃናትም ገና በአካልና በአእምሮ በማደግ ላይ ያሉ በመሆናቸው ምክንያት ለጥቃት ተጋላጮች ናቸው:: በሕፃናት ላይ የሚፈጸም ጥቃት በአእምሮአቸውና በአካላቸው ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ጥቃቶችን፣ ወሲባዊ ጥቃትን፣ እንግልትን፣ ክብራቸውን፣ ደኅንነታቸውን እና ነጻነታቸውን የሚጎዱ የመብቶች አያያዞችን ይጨምራል:: በመሆኑም ሴቶች እና ሕፃናት ጤንነታቸውን፣ አካላቸውን፣ አእምሮአቸውን እንዲሁም ማኅበራዊ እድገታቸውን በተመለከተ ልዩ ጥበቃ የሚሹ በመሆናቸው ክብራቸውን፣ ደኅንነታቸውን እና ነጻነታቸውን መሠረት ያደረገ ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል::

የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት ለደረሰባቸው ጥቃት መፍትሔ ፍለጋ በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ በሚያልፉበት ጊዜ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ምላሽ አሰጣጥ በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ማዕቀፎች የተጠበቁላቸውን መብቶች ባከበረ መልኩ ሊሆን ይገባል:: የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ምላሽ አሰጣጥ የተጎጂዎችን ሰብአዊ መብቶች ማእከል ያደረገ መሆን፣ የጥቃት አድራሹን ተጠያቂነት እና የተጎጂዎችን ፍትሕ የማግኘት መብት እንዲረጋገጥ ከማድረጉም በላይ የጥቃት

[1] CEDAW General Recommendation no 19: Violence against women,1992 (hereinafter referred to as ‘CEDAW 19’); Declaration on the Elimination of Violence against Women (hereinafter referred to as ‘DEVAW’), Article 1 and 2

ተጎጂ የሆኑ ሴቶችና ሕፃናት በፍትሕ ሥርዓቱ የሚኖራቸውን እምነት በማሳደግ ረገድ የጎላ ሚና ይኖረዋል፡፡ ሆኖም በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት በተደራሽነት ችግሮች፣ የአሠራር ክፍተቶች እንዲሁም ሴቶች እና ሕፃናትን አስመልክቶ ያሉ የተዛቡ አመለካከቶች የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ሲያልፉ ለሁለተኛ ደረጃ ጥቃት እና ለሰብአዊ መብቶች ጥሰት እንዲጋለጡ ከማድረግ በተጨማሪ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱን ታማኝነት እና ገለልተኝነት ጥያቄ ውስጥ ይከታሉ፡፡

በዚህ መሠረት ኮሚሽኑ በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ውስጥ የጥቃት ተጎጂ የሆኑ ሴቶችና ሕፃናት መብቶች አያያዝ ሁኔታን ለመፈተሽ ከሚያዚያ 30 ቀን 2015 ዓ.ም. እስከ ግንቦት 4 ቀን 2015 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ በሰባት ክፍለ ከተሞች (አቃቂ፣ አራዳ፣ ቦሌ፣ ንፋስ ስልክ፣ ልደታ፣ ቂርቆስ እና ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማዎች) እና በኦሮሚያ ክልል በሸገር ከተማ አስተዳደር፣ በቡራዩ እና ሰበታ ክፍለ ከተማዎች፣ እንዲሁም ከሐምሌ 29 እስከ ነሐሴ 8 ቀን 2015 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን፣ ጅማ ከተማ እና በሸቤ ሶምቦ ወረዳ፣ በሐረሪ ክልል፣ በሐረር ከተማ እና በኤረር ወረዳ በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር የጥቃት ተጎጂ ሴቶች እና ሕፃናት መብቶች አያያዝ ላይ ክትትል አከናውኗል፡፡ እነዚህ አካባቢዎች የተመረጡበት ምክንያትም አዲስ አበባ የፌዴራል የፍትሕ ተቋማት የሚገኙበት በመሆኑ፤ በኦሮሚያ ክልል በሸገር ከተማ አስተዳደር የቡራዩ እና የሰበታ ክፍለ ከተማዎች በክልሎች ለሚደረገው ክትትል መነሻ ግብአት እንዲሆን ሲሆን የሐረሪ ክልል እና የጅማ ዞን ተቋማት ለክትትሉ ከተመረጡት ክልሎች በወቅቱ አንጻራዊ ሰላም በመኖሩ ምክንያት ነው፡፡

## 1.2 የክትትሉ ዓላማ

የክትትሉ ዓላማ በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ውስጥ የጥቃት ተጎጂ የሆኑ ሴቶች እና ሕፃናት መብቶች አያያዝን ከዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊ እና ሀገር አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ማዕቀፎች አንጻር መቃኘት ነው፡፡ በዚህ አግባብ ተጎጂዎች የተፈጸመባቸውን ወንጀል ከማመልከት ጀምሮ በጠቅላላው የወንጀል ፍትሕ ሂደት የሚያልፉባቸውን ሁኔታዎች እና በምላሽ አሰጣጥ የሚታዩ የመብቶች ጥሰቶችን ከነመነሻ ምክንያቶቻቸው ለመለየት ያለመ ነው፡፡

## 1.3 የክትትሉ ወሰን

ክትትሉ የጥቃት ተጎጂ ሴቶች እና ሕፃናት በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ውስጥ ከአቤቱታ አቀራረብ ሥርዓት ጀምሮ፣ በምርመራ ሂደት፣ በክስ አቀራረብና አሰማም፣ እንዲሁም በፍርድ ወቅት ያላቸው የመብቶች አያያዝ በዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊ እና በሀገር አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ማዕቀፎች ከተጠበቁላቸው የሰብአዊ መብቶች መስፈርቶች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን መፈተሽ ላይ የተገደበ ነው፡፡

ክትትሉ የተከናወነው በአዲስ አበባ ከተማ አቃቂ፣ አራዳ፣ ቦሌ፣ ንፋስ ስልክ፣ ልደታ፣ ቂርቆስ እና ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተሞች፣ በኦሮሚያ ክልል በሸገር ከተማ አስተዳደር በቡራዩ እና ሰበታ ክፍለ ከተሞች፣ በጅማ ዞን ጅማ ከተማ እና ሸቤ ሶምቦ አዋሳኝ ወረዳ፣ እንዲሁም በሐረሪ ክልል በሐረር ከተማ እና በኤረር አዋሳኝ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ የፍትሕ፣ የድጋፍ እና የመጠለያ

ተቋማት ነው። በአዲስ አበባ ከተማ ክትትል የተካሄደባቸው ሰባቱ ክፍለ ከተሞች የተመረጡት የፌዴራል የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች፣ የሴቶች እና የሕፃናት ልዩ ችሎት፣ እንዲሁም በከተማው የሚገኙት የአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ የጤና ተቋማት የሚገኙባቸው በመሆናቸው ነው።

በአዲስ አበባ ከተማ ሰባት ክፍለ ከተሞች እና በሸገር ከተማ አስተዳደር በቡራዩ እና ሰበታ ክፍለ ከተሞች የተከናወነው ክትትል የወሲባዊ ጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት የመብቶች አያያዝ ላይ ብቻ ያተኮረ ነው። በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን እና በሸቤ ሶምቦ አዋሳኝ ወረዳ፣ እንዲሁም በሐረሪ ክልል በሐረር ከተማ እና በኤረር አዋሳኝ ወረዳ የተከናወነው ክትትል በተለያየ የጥቃት አይነት ተጎጂ የሆኑ ሴቶችና ሕፃናት በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ያላቸውን የመብቶች አያያዝ የተመለከተ ነው።

## 1.4 የክትትሉ አስፈላጊነት

በኢትዮጵያ የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ሲያልፉ በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ማዕቀፎች የተጠበቁላቸውን መብቶች ለመተግበር፣ በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን በቅንጅት ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት ብሔራዊ ስትራቴጂ ተቀርጾ ለመተግበር የተደረጉ ጥረቶች ነበሩ። ሆኖም የሲዳው ኮሚቴ በስምንተኛው ወቅታዊ ግምገማ ለኢትዮጵያ በሰጠው ምክረ ሐሳብ፤ የብሔራዊ ስትራቴጂው አፈጻጸም ተጨባጭ ውጤት አለማምጣቱን እና ለዳኞች፣ ለዐቃቤያነ ሕግ፣ ለፖሊስ አባላት እንዲሁም ለሕግ አስፈጻሚ አካላት ጾታን መሠረት ስላደረገ ጥቃት በቂ ስልጠና አለመሰጠቱን ገልጿል። ኢትዮጵያ ለጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት የተቀናጀ እና ዘርፈ ብዙ ምላሽ መስጠት ለማስቻል የተዘጋጀውን የስትራተጂክ ዕቅድ አፈጻጸም እንድታሻሽል እንዲሁም በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ የጥቃት ወንጀሎች ላይ ለሚሠሩ ዳኞች፣ ለዐቃቤያነ ሕግ፣ የፖሊስ አባላት እንዲሁም ለሌሎች ሕግ አስፈጻሚ አካላት የሴቶች ሰብአዊ መብቶችን እና ጾታ ተኮር የምርመራ ሥርዓትን አስመልክቶ በቂ ስልጠና እንዲሰጥ የሲዳው ኮሚቴ ምክረ- ሐሳብ አቅርቧል።[2]

የሕፃናት መብቶች ኮሚቴ በአራተኛው እና በአምስተኛው ወቅታዊ ግምገማ በኢትዮጵያ ጥቃት አድራሾችን ተጠያቂ ያለማድረግ ችግሮች እንዲሁም ለተጎጂ ሕፃናት በቂ የማገገሚያ አገልግሎቶች አለመኖር እንዳሳሰበው ገልጾ የጾታዊ ጥቃትን አስመልክቶ ክትትል የማድረግ፣ ምርመራ የማከናወን እና ክስ የመመስረት ኃላፊነት ያለባቸው ተቋማት ለሕፃናት የጥቃት ተጎጂዎች በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆኑ ምክረ ሐሳብ አስቀምጧል።[3] በተመሳሳይ የአፍሪካ ሕፃናት መብቶችና ደህንነት ኮሚቴ ኢትዮጵያ በሕፃናት ላይ ጥቃት የሚፈጽሙ ወንጀለኞችን ተጠያቂ እንድታደርግ እንዲሁም

---

[2] Concluding observations on the eighth periodic report of Ethiopia, adopted by the CEDAW Committee at its Seventy-second session ( 18 February-8 March 2019), paragraphs 23(b) and 24(D and E)

[3] Concluding observations on the combined fourth and fifth periodic reports of Ethiopia, Adopted by the Committee on the Rights of the Child, at its sixty-ninth session (18 May—5 June 2015, Paragraph 43 and 44

በሕፃናት ጥቃት ዙሪያ ምርመራ እና ክትትል የሚያደርጉ ልዩ የፖሊስ አባላትን አቅም የማሳደግ ሥራዎችን እንድትቀጥል በአንቀጽ 23 ምክረ ሐሳብ ሰጥቷል፡፡[4]

በተጨማሪም የሕፃናት ጥቃትን የተመለከቱ አቤቱታዎችን ለመቀበል፣ ለመቆጣጠር፣ ለመመርመርና ጥፋተኞችን ለመክሰስ የሚያስችሉ ውጤታማ የአሠራር ሥርዓቶችንና መንገዶችን ለመዘርጋት የሚደረጉ ጥረቶችን በእጥፍ እንድታሳድግ፣ በሕፃናት ላይ ጥቃት የፈጸሙ ሰዎች ተገቢው ክስ እንደተመሰረተባቸው ማረጋገጥና ምቹ ያልሆነ አያያዝና ጉዳትን በሚገባ ለመለየት፣ ሪፖርት ለማድረግና ለማስተደደር የሚያስችሉ የስልጠና ፕሮግራሞችን እንድትቀርጽ በ3ኛው ዙር የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት ሁሉን አቀፍ ወቅታዊ የግምገማ መድረክ (Universal Periodic Review-UPR) በአንቀጽ 151 እና 159 ምክረ-ሐሳብ አቅርቧል፡፡[5] በአጠቃላይ በዓለም አቀፍ እና በአህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ኮሚቴዎች ለኢትዮጵያ የተሰጡ ጠቅላላ ምክረ ሐሳቦች፣ የመንግሥት ይፋዊ ሪፖርቶች፣ በዓለም አቀፍ ተቋማት እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወጡ የጥናት ውጤቶች እንዲሁም መገናኛ ብዙኃን በተለያየ ጊዜ ያወጧቸው ዘገባዎች በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር የጥቃት ተጎጂ የሆኑ ሴቶች እና ሕፃናት መብቶች አያያዝ ሁኔታ አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሰ መሆኑን ያመላክታሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ኮሚሽኑ በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ውስጥ የጥቃት ተጎጂ ሴቶች እና ሕፃናት መብቶች አያያዝ በዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊ እና ሀገር አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መመዘኛዎች መሠረት እየተተገበሩ ስለመሆኑ ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

## 1.5 የክትትሉ ሥነ-ዘዴ

ኮሚሽኑ ለክትትሉ የሚከተሉትን ዝርዝር የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ተጠቅሟል፡፡

1. **የሕግ ትንተና፡-** ይህንን ዘዴ በመጠቀም ከአቤቱታ አቀራረብ ሥርዓት ጀምሮ፣ በምርመራ ሂደት፣ በክስ አቀራረብ እና አሰማም፣ እንዲሁም በድኅረ-ችሎት በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ሂደት ውስጥ ለጥቃት ተጎጂ ሴቶች እና ሕፃናት ጥበቃ የሚያደርጉ ዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊ እና ሀገራዊ የሰብአዊ መብቶች ማዕቀፎች ተመርምረዋል፡፡ አግባብነት ያላቸው ሀገራዊ የሕግ እና የፖሊሲ ማዕቀፎችም ታይተዋል፡፡
2. **ቃለ መጠይቅ፡-** ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፍትሕ ተቋማት፣ የተቀናጀ የአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ማእከላት እና የተጎጂዎች መጠለያ ተቋማት ኃላፊዎች እንዲሁም መጠለያ ተቋማት ውስጥ ከሚገኙ የወሲባዊ ጥቃት ተጎጂ ሴቶች እና ሕፃናት በቃለ መጠይቅ መረጃ ተሰብስቧል፡፡

[4] Concluding recommendations by the African Committee of Experts on the Rights and welfare of the Child (ACERWC) on the Federal democratic republic of Ethiopia's report on the status of implementation of the African Charter on the Rights and welfare of the Child.

[5] በተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት ሁሉን አቀፍ ወቅታዊ የግምገማ መድረክ (Universal Periodic Review /UPR) ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የተሰጡ ምክረ ሐሳቦች 3ኛ ዑደት — 33ኛ ክፍለ ጊዜ ግንቦት ወር 2011 ዓ.ም.

3. **ምልከታ፡-** የፍትሕ እና ድጋፍ ሰጪ ተቋማት ከባቢያዊ ሁኔታ እና አሠራሮች ላይ ከጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት መብቶች አያያዝ አንጻር ምልከታ ተደርጓል፡፡
4. **የቡድን ውይይት፦** የወሲብ ጥቃት ተጎጂ ከሆኑ ሴት ሕፃናት ጋር ተገቢው ጥንቃቄ የተደረገበት የቡድን ውይይት ተደርጓል፡፡
5. **የምክክር መድረክ፡-** የክትትሉን ረቂቅ ሪፖርት ባለድርሻ አካላት በተገኙበት የምክክር መድረክ ላይ በማቅረብ ተጨማሪ ግብአቶች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

በዚህ ክትትል በአጠቃላይ 102 ሰዎች የተሳተፉበት ሲሆን፣ እነዚህም 24 ዳኞች፣ 18 ዐቃቤያነ ሕግ፣ 23 ፖሊሶች፣ 8 የተቀናጀ የአንድ ማእከል ባለሙያዎች፣ 4 የመጠለያ ተቋማት ባለሙያዎች ፣ 3 በፍርድ ቤት የሚገኙ የማኅበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች እና 22 የጥቃት ተጎጂዎች ናቸው፡፡ በእያንዳንዱ የክትትል ቦታ የተሳተፉትን በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

| መረጃ የሰጡ አካላት | አዲስ አበባ | ሐረር | ጅማ | በሸገር ከተማ አስተዳደር የቡራዩ እና ሰበታ ክፍለ ከተሞች | አጠቃላይ |
|---|---|---|---|---|---|
| ፖሊስ | 14 | 3 | 4 | 2 | 23 |
| ዐቃቤያነ ሕግ | 9 | 4 | 3 | 2 | 18 |
| ዳኞች | 15 | 4 | 3 | 2 | 24 |
| የተቀናጀ የአንድ ማከል ባለሙያዎች | 5 | 2 | 1 | 0 | 8 |
| በፍርድ ቤት የሚገኙ የማኅበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች | 3 | 0 | 0 | 0 | 3 |
| የጥቃት ተጎጂዎች | 15 (4 ለአካለ መጠን የደረሱ ሴት እና 11 ሴት ሕፃናት) | 0 | 7 ሴት ሕፃናት | 0 | 22 |
| ከመጠለያ ተቋማት ባለሙያዎች | 3 | | | 1 | 4 |
| | | | | | **102** |

## 1.6 የክትትሉ ውስንነቶች

ኮሚሽኑ ክትትሉን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እንዲሁም በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና በሲዳማ ክልሎች የሁሉም ዐይነት የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ያላቸውን መብቶች አያያዝ በተመለከተ ለማከናወን ያቀደ ቢሆንም በወቅቱ በነበረው የጸጥታ ችግር በእነዚህ ቦታዎች ሁሉ ክትትሉን ማከናወን አልቻለም፡፡ በአዲስ አበባ ከተማም የተመረጡት የፍትሕ ተቋማት የሥራ ክፍሎች ሁሉንም ዐይነት ጥቃቶች የሚያዩ ሳይሆኑ በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ወሲባዊ ጥቃቶችን ብቻ የሚያስተናግዱ በመሆኑ የክትትሉን ወሰን የወሲባዊ ጥቃት ተጎጂዎች የመብቶች አያያዝ ላይ ብቻ እንዲሆን አድርጓል፡፡

በክትትሉ ከተዳሰሱት የመብቶች አተገባበር አንዱ ፍትሕ የማግኘት መብት ሲሆን ይህ መብት መገለጫዎቹ ዘርፈ ብዙ እና ከበርካታ መብቶች አተገባበር ጋር የተያያዘ ቢሆንም በጊዜ እና በበጀት ውስንነት ምክንያት ክትትሉ ፍትሕ የማግኘት መብት አንዱ መገለጫ በሆነው የፍትሕ ተቋማት ተደራሽነት ላይ ብቻ ትኩረት አድርጓል፡፡

## ክፍል ሁለት

## አግባብነት ያላቸው የሕግ እና የፖሊሲ ማዕቀፎች

### 2.1 የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ያላቸው መብቶች በዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች እና ሰነዶች

የጥቃት ተጎጂ ሴቶች እና ሕፃናት በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ውስጥ ያላቸውን መብቶች የሚመለከቱ የተለያዩ ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ ስምምነቶችና ሰነዶች አሉ፡፡

ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸው በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውንም አድሎአዊ ልዩነት ለማስወገድ የተደረገ ስምምነት (CEDAW/ሲዳው)፣ በሴቶች ላይ የሚደረግ አድሎአዊ ልዩነት ለማስወገድ የተቋቋመው ኮሚቴ (የሲዳው ኮሚቴ) አጠቃላይ ምክረ ሐሳብ ቁጥር 19፣ 33 እና 35፣[6] የሕፃናት መብቶች ስምምነት፣ የአፍሪካ የሕፃናት መብቶችና ደኅንነት ቻርተር፣ የአፍሪካ የሰዎች እና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር፣ የአፍሪካ የሴቶች መብቶች ፕሮቶኮል (የማፑቶ ፕሮቶኮል)፣ ዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት፣ ሕፃናትን ለወሲብ ንግድ ማሰማራት እና የወሲብ ፊልም ማሠራትን ለማስወገድ የተደረገ አማራጭ ፕሮቶኮል እንዲሁም የጥቃት ተጎጂ ሴቶች እና ሕፃናትን መብቶች አያያዝን አስመልክተው የወጡ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሰነዶች ናቸው፡፡ በተጨማሪም የቤጂንግ የድርጊት መርኃ ግብር፣ የወንጀል እና ሥልጣንን አላግባብ የመጠቀም ተጎጂ ለሆኑ ሰዎች የወጣው የተባበሩት መንግሥታት የፍትሕ መሠረታዊ መርሖች መግለጫ(UN Declaration of Basic Principles of Justice for Victims of Crime and Abuse of Power)፣ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለማስወገድ የወንጀል መከላከል እና የወንጀል ፍትሕ እርምጃዎች ላይ በጠቅላላ ጉባኤው የተሰጡ ውሳኔዎች (General assembly resolution 52/86 on crime prevention and criminal justice measures to eliminate violence against women)፣ የተባበሩት መንግሥታት ሕፃናት የወንጀል ተጎጂዎችን እና ምስክሮችን የሚያሳትፉ ጉዳዮች ፍትሕ መመሪያ ( UN ECOSOC (economic and social council) resolution 2005/20 Guidelines on justice in matters involving child victims and witnesses of crime)፣ እና በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለማስወገድ የወጣው የተባበሩት መንግሥታት መግለጫ ይገኙበታል፡፡

እነዚህ ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ ስምምነቶችና ሰነዶች የጥቃት ተጎጂ የሆኑ ሴቶች እና ሕፃናት ተደራሽ የሆነ ፍትሕ የማግኘት፣ ክብርን በጠበቀ እና ምስጢራዊነቱ በተጠበቀ የፍትሕ ሥርዓት የመስተናገድ፣ ከሁለተኛ ደረጃ ጥቃት (secondary victimization) የመጠበቅ፣ የተፋጠነ ፍትሕ እና ውጤታማ መፍትሔ የማግኘት፣ የመሰማት፣ የደኅንነት ጥበቃና ድጋፍ የማግኘት መብቶች

[6] የኮሚቴው አጠቃላይ ምክረ ሐሳብ ቁ. 35 አስቀድሞ በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃትን አስመልክቶ የተሰጠውን አጠቃላይ ምክረ ሐሳብ ቁ. 19 ለማሻሻል (update ለማድረግ) በተመሳሳይ ርዕሠ ጉዳይ ላይ የተሰጠ ምክረ ሐሳብ ነው፡፡

እንዳሏቸው ይደነግጋሉ። መንግሥትም ይህንን የማክበር፣ የማስጠበቅ እና የማሟላት ተነፃፃሪ ግዴታ እንዳለበት ያብራራሉ።

### 2.1.1 ፍትሕ የማግኘት መብት

ፍትሕ የማግኘት መብት የሕግ የበላይነት መገለጫ እና ለሌሎች መብቶች መከበር መሠረት ነው።[7] ፍትሕ የማግኘት መብት መገለጫዎቹ ዘርፈ ብዙ እና ከበርካታ መብቶች አተገባበር ጋር የተያያዘ ሲሆን የፍትሕ ተቋማት ተደራሽነት አንዱ መገለጫ ነው። ተደራሽ የሆነ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ለሁሉም የማኅበረሰብ ክፍሎች ያለምንም አድልዎ እኩል የሆነ የፍትሕ አገልግሎት መስጠት መቻል ነው። ይህም ማለት የፍትሕ ተቋማት አገልግሎት ብዝኃ ፍላጎቶችን እንዲሁም ዐይነተኛ ተግዳሮቶች ያሉባቸው ሴቶችና ሕፃናትን፣ በተለይም አካል ጉዳተኛ እና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ታሳቢ ያደረጉ ሊሆኑ ይገባል።

የሴቶች ፍትሕ የማግኘት መብትን በተመለከተ የወጣው የሲዳው ኮሚቴ ምክረ ሐሳብ ቁጥር 33 የሲዳው ፈራሚ ሀገራት ለሁሉም የማኅበረሰብ ክፍሎች ያለ ምንም አድልዎ ተደራሽ የሆነ የፍትሕ ሥርዓት እንዲተገብሩ በአንቀጽ 14(ለ) እና (ሐ)፣ 16(ሀ)፣ እና 17(ለ)(ሰ) ተመላክቷል።

የፍትሕ ተደራሽነት የፍትሕ እና የድጋፍ ሰጪ ተቋማት ኢኮኖሚያዊ ተደራሽነትን (economic accessibility) ፣ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ መሆንን፣ የቋንቋ እና የመረጃ ተደራሽነትን ይጨምራል። ኢኮኖሚያዊ ተደራሽነት የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ለሁሉም ማኅበረሰብ በቅርበት የሚገኙ ወይም የተቋማትን አገልግሎት ለማግኘት በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚኖሩ የማኅበረሰብ ክፍሎችን የመጓጓዣ ወጪ የማያስወጡ ወይም የጊዜ እና የመጓጓዣ ወጪዎች በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚኖሩ የማኅበረብ ክፍሎችን ዐቅም ያገናዘቡ_መሆናቸውን ይጨምራል። በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት የፖሊስ ጣቢያዎችን (መምሪያዎች)፣ የዐቃቤያነ ሕግ ጽሕፈት ቤቶች፣ ፍርድ ቤቶች፣ የሕክምና ማስረጃ የሚያቀርቡ የጤና ተቋማት፣ የሥነ-ልቦና አገልግሎት መስጫ ተቋማት እና የመጠለያ ተቋማትን ያካትታል። የተጠቀሱትን የተለያዩ አገልግሎቶች በተለያዩ ተቋማት ለማግኘት ያለውን እንግልት፣ ምልልስ እና የመጓጓዣ ወጪ ለመቀነስ፣ ሀገራት ሴት የጥቃት ተጎጂዎች ሁሉንም አገልግሎቶች በአንድ ቦታ እንዲያገኙ የሚያስችላቸውን የተቀናጀ የአንድ ማእከል አገልግሎት እንዲያቋቁሙ እና እነዚህ የተቀናጀ የአንድ ማእከል አገልግሎት ተቋማት ለሁሉም ሴቶች ተደራሽ መሆን እንደሚኖርባቸው በሲዳው ኮሚቴ ምክረ ሐሳብ ቁጥር 33 አንቀጽ 17(ረ) ተገልጿል።

ሌላው የፍትሕ ተቋማት ተደራሽነት መገለጫ የፍትሕ ተቋማት የሕንጻ አሠራር እና አገልግሎት አሰጣጥ አካል ጉዳተኛ የጥቃት ተጎጂዎችን ፍላጎት ያማከለ መሆን ነው። ሀገራት የአካል ጉዳተኞችን ፍትሕ የማግኘት መብት ለማረጋገጥ የፍትሕ እና የድጋፍ ሰጪ ተቋማት የሕንጻ አሠራር እና አገልግሎት አሰጣጥ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆኑ አስፈላጊውን መገልገያዎች እና አገልግሎቶች እንዲያቀርቡ የዓለም አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት ያስገድዳል።

[7] See the introduction part of CEDAW General Recommendation No. 33 on women's access to justice, 2015 (hereinafter referred to as 'CEDAW 33')

[8] የፍትሕ እና የድጋፍ ሰጪ ተቋማት የሕንጻ አሠራር እና አገልግሎት አሰጣጥ አካል ጉዳተኛ እና ጉዳት አልባ የጥቃት ተጎጂዎችን እኩል አገልግሎት መስጠት የሚያስችል መሆን አለበት፡፡ በመሆኑም የፍትሕ ተቋማት መግቢያ በሮች፣ ቢሮዎች፣ የችሎት አዳራሾች፣ መጸዳጃ ቤቶች እና መተላለፊያ መንገዶች የአካል ጉዳተኛ ተጠቃሚዎችን ፍላጎቶች ያማከሉ ሊሆኑ ይገባል፡፡

የመረጃ ተደራሽነት ሌላኛው የፍትሕ ተደራሽነት ማሳያ ነው፡፡ ይህም ማለት ተጎጂዎች በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት በሚያልፉበት ጊዜ ስለሚኖራቸው መብቶች፣ ስለ ወንጀል ፍትሕ ሥነ ሥርዓት አካሄድ፣ ሊያገኟቸው ስለሚገቡ የሕግ መፍትሔዎች እንዲሁም የሕክምና፣ የሥነ ልቦና፣ የማኅበራዊ አገልግሎቶች እና መሰል መረጃዎችን በሚረዱት ቋንቋ መረጃ የማግኘት መብት ነው፡፡ [9] በተጨማሪም በአካል ጉዳት፣ የመደበኛ ትምህርት ባለማግኘት ምክንያት፣ እንዲሁም የፍትሕ ተቋማትን የሥራ ቋንቋን መረዳት ባለመቻላቸው ምክንያት ተደራራቢ ተጋላጭነት ላለባቸው የጥቃት ተጎጂ ሴቶች መጠቀም ስለሚችሉት የሕግ እና የማኅበራዊ አገልግሎቶች በሚረዱት ቋንቋ መረጃ የማግኘት መብት እንዳለቸው እና መንግሥትም መረጃውን የማሰራጨት ግዴታ እንዳለበት የሲዳው ኮሚቴ ምክረ ሐሳብ ቁጥር 35 አንቀጽ 43 ይጠቅሳል፡፡

የፍትሕ እና የድጋፍ ሰጪ ተቋማት ለሥራ ከሚጠቀሙባቸው የሥራ ቋንቋዎች ውጪ ለሚናገሩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ተደራሽ መሆን አንዱ የተደራሽነት መገለጫ ነው፡፡ ይህም ማለት የፍትሕ እና የድጋፍ ሰጪ ተቋማትን የሥራ ቋንቋ መረዳት የማይችሉ ሰዎች የተቋማቱ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ፣ እነዚህ ተቋማት የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚን[10] ጨምሮ የትርጉም ባለሙያ ወይም አስተርጓሚ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

### 2.1.2 ክብርን በጠበቀ እና ለሁለተኛ ደረጃ ጥቃት በማያጋልጥ መልኩ የመስተናገድ መብት

የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ሲያልፉ ክብራቸውን በጠበቀ እና ለሁለተኛ ደረጃ ጥቃት በማያጋልጥ መልኩ የመስተናገድ መብት አላቸው፡፡ እነዚህ መብቶች ተቀራራቢ እና ተደጋጋፊ ናቸው፡፡ ሁለተኛ ደረጃ ጥቃት ማለት የጥቃት ተጎጂ የሆኑ ሴቶችና ሕፃናት ከደረሰባቸው ጥቃት በተጨማሪ በፍትሕ እና በድጋፍ ሰጪ ተቋማት ወይም በግለሰቦች በሚሰጣቸው ተገቢ ያልሆኑ ምላሾች ወይም ለደረሰባቸው አካላዊና ሥነልቦናዊ ጉዳት ምቹ የሆነ አገልግሎት ባለመኖሩ ወይም የጉዳዩን ልዩ ጠባይ ከግምት በማስገባት የሚደረግ የተሟላ አገልግሎት ባለመኖሩ የተነሳ ለተጨማሪ ሥነልቦናዊ ስቃይና ጉዳት ወይም ለዳግም ጥቃት መጋለጥ ነው፡፡ የጥቃት ተጎጂዎች በተደጋጋሚ ከጥቃት አድራሹ ተጠርጣሪ ጋር በፍትሕ ሂደት መገናኘት፣ በተመሳሳይ ወይም በተለያዩ የፍትሕ አካላት በተደጋጋሚ ቃል መጠይቅ መደረግ፣ በፍትሕ አካላት የሚሰጣቸው ተገቢ ያልሆኑ አስተያየቶች ወይም አመለካከቶች የጥቃት

[8] Convention on the rights of persons with disabilities (hereinafter referred to as ‘CRPD’) Principle 2

[9] CEDAW 33, paragraph 11 and paragraph 17©, UN declaration of basic principles of justice for victims of crime and abuse of power, 1985 (hereinafter referred to as ‘Basic principles of justice for victims of crime and abuse of power’), Article 5 and 15.

[10] CEDAW 33, paragraph 17(a)

ተጎጂዎችን ለሁለተኛ ደረጃ ጥቃት፣ ስቃይ እና የሥነልቦና ጉዳት ብሎም ለዳግም ጥቃት ያጋልጧቸዋል:: በክብር አለመስተናገድ ወይም ያልተገባ ምላሽ አሰጣጥም ተጎጂዎቹን ለሁለተኛ ደረጃ ጥቃት ወይም ጉዳት የሚያጋልጥ ነው:: ማኅበረሰቡ ለሴቶች በተለይም ለጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት ያለው ተገቢ ያልሆነ አመለካከት በፍትሕ ባለሙያዎችም እንደሚንጸባረቅ የሲዳው ኮሚቴ ምክረ ሐሳብ ቁጥር 33 ይገልጻል::[11]

የወንጀል እና ሥልጣንን አላግባብ የመጠቀም ተጎጂ ለሆኑ ሰዎች የወጣው የተባበሩት መንግሥታት የፍትሕ መሠረታዊ መርሖዎች መግለጫ አንቀጽ 4 ተጎጂዎች ክብራቸውን በጠበቀ መልኩ የመያዝ እና የመስተናገድ መብት እንዳላቸው ይደነግጋል:: በክብር መያዝ ወይም መስተናገድ የሰው ልጅ መሠረታዊ መብት ነው፤ ይኸው መብት የጥቃት ተጎጂ የሆኑ ሴቶች እና ሕፃናት በወንጀል ፍትሕ አስተዳደር በሚያልፉበት ጊዜም ተፈጻሚ ይሆናል:: በተመሳሳይ የአፍሪካ የሴቶች መብቶች ፕሮቶኮል (የማፑቶ ፕሮቶኮል) አንቀጽ 3 ሀገራት የሴቶችን ክብር የማስከበር ግዴታ እንዳለባቸው ይደነግጋል:: የሲዳው ኮሚቴ ምክረ ሐሳብ ቁጥር 33 አንቀጽ 51(ሐ)፣ 51 (መ)፣ 15(ሀ) እና 15(ሐ)፣ የቤጂንግ የድርጊት መርኃ ግብር አንቀጽ 124(ሰ) እና 232(ቸ) እንዲሁም የአፍሪካ የሕፃናት መብቶችና ደኅንነት ቻርተር ኮሚቴ ኢትዮጵያ የጥቃት ተጎጂ ሕፃናት በፍትሕ ሥርዓቱ በሚኖራቸው ግንኙነት ለሁለተኛ ደረጃ ጥቃት እንዳይጋለጡ እርምጃ መውሰድ እንደሚጠበቅባት በምክረ ሐሳባቸው ገልጸዋል[12]::

የጥቃት ተጎጂዎች በፍትሕ ሥርዓቱ ክብራቸው በተጠበቀ መልኩ የመስተናገድ መብታቸው እንዲተገበር እና ለሁለተኛ ደረጃ ብሎም ለዳግም ጥቃት እንዳይጋለጡ ሀገራት ከሚጠበቅባቸው እርምጃዎች አንዱ የፍትሕ አካላትን ባለሙያዎች ፖሊስ፣ ዐቃቤያነ ሕግን፣ ዳኞችን እና የድጋፍ አገልግሎት ሰጪ ባለሙያዎችን ከፍረጃ እና አግባብ ካልሆኑ አመለካከት እንዲታቀቡ፤ በሴቶችና ሕፃናት ላይ ስለሚፈጸሙ ጥቃቶች እና ምላሽ አሰጣጥ፣ እንዲሁም ስለ ሰብአዊ መብቶች ግንዛቤ እንዲኖራቸው ስልጠና መስጠት እንደሚገባ የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሰነዶች ይደነግጋሉ:: [13] በተጨማሪም በፍትሕ ሥርዓቱ የሕፃናትን ጥቃቶች ጉዳይ የሚመለከቱ ባለሙያዎች በሕፃናት መብቶች ላይ የሰለጠኑ እንዲሆኑ የሲዳው ኮሚቴ ምክረ ሐሳብ ቁጥር 33 አንቀጽ 13 ይደነግጋል:: ስለሆነም የፖሊስ ተቋማት፣ የዐቃቤያነ ሕግ ተቋማት፣ ፍርድ ቤቶች እና የድጋፍ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ምላሽ አሰጣጥ የጥቃት ተጎጂ ሴቶች እና ሕፃናትን ክብራቸውን የሚጠብቅ እና ለሁለተኛ ደረጃ እና ለዳግም ጥቃት የማያጋልጥ መሆን ይኖርበታል:: የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት በፖሊስ፣ በዐቃቤያነ ሕግ ጽሕፈት ቤቶች፣ በፍርድ ቤቶች እና በድጋፍ ሰጪ ተቋማት

---

[11] CEDAW 33, paragraph 26

[12] Concluding recommendations by the African Committee of experts on the rights and welfare of the child (ACERWC) on the Federal Democratic Republic of Ethiopia's report on the statuts of implementation of the African Charter on the Rights and Welfare of the Child

[13] CEDAW, article 2(f) and 5(a); CEDAW 33, paragraph 26,27, and 1(5)a; Maputo Protocol, article 4(2), and (4(d); General assembly resolution on crime prevention and criminal justice measures to eliminate violence against women,1998 (hereinafter referred to as 'resolution on crime prevention and criminal justice measures') parag 8 and 12.

በሚቀርቡበት ጊዜ የደረሰባቸውን ጉዳት የማቅለል፣ የመፈረጅ፣ ለጥቃቱ መከሰት ተጎጂዎችን ጥፋተኛ የማድረግ፣ የማመናጨቅ እንዲሁም ያለ በቂ ምክንያት አመኔታን መንፈግ የመሰሉ አስተያየቶችና አመለካከቶች የተጎጂዎችን ሰብአዊ ክብር እና የጉዳታቸውን ልዩ ሁኔታ ከግምት የማያስገባ ስለሆነ ለሁለተኛ ደረጃ ጥቃት እና አልፎም ለዳግም ጥቃት ያጋልጣል፡፡

## 2.1.3 ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ የፍትሕ አገልግሎት የማግኘት መብት

የአቤቱታ ማመልከቻ ሥርዓት፣[14] የምርመራ አካሄድ፣[15] እንዲሁም የችሎት ሂደት[16] ምስጢራዊነቱን እና የተጎጂዎችን ደኅንነት ባስጠበቀ መልኩ ሊካሄድ እንደሚገባ እና በዚህም አግባብ የአቤቱታው አቀራረብ ሥርዓት፣ የምርመራ ሥራ እና የችሎት ሂደት የተጎጂዋን ማንነት፣ የቀድሞ ታሪክ፣ ስለተፈጸመው ጥቃት እና ሌሎች መረጃዎች ምስጢራዊነታቸው በተጠበቀ መልኩ ሊከናወን እንደሚገባ በሲዳው ኮሚቴ ምክረ ሐሳብ 33 በቁጥር 18(ሰ)(ረ) እና 51 እንዲሁም በቤጂንግ የድርጊት መርኃ ግብር ላይ ተገልጿል፡፡

ምስጢራዊነቱ እና ደኅንነቱ የተጠበቀ የፍትሕ ሥርዓት መገለጫዎቹ በርካታ እና ዝርዝር ቢሆኑም አቤቱታ የሚቀርብባቸው እና ምርመራ የሚደረግባቸው ክፍሎች የተለዩ መሆን፣ ከተጎጂዋ/ው እና ከአቤቱታ ተቀባይ ወይም መርማሪ ፖሊስ ውጪ ለሌላ ሦስተኛ ወገን ዝግ የሆነ መሆን፣ ከሦስተኛ ወገን ዕይታ የራቀ፣ ተጎጂዎች ያለ ምንም ፍርሀት በነጻነት ጉዳያቸውን እንዲያስረዱ የሚያስችል የአቤቱታ መቀበያ እና የምርመራ ክፍሎች መኖር ምስጢራዊነቱ እና ደኅንነቱ የተጠበቀ የፍትሕ ሥርዓት እንዲኖር የሚያስችሉ ናቸው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በችሎት ሂደት ጊዜ ችሎቱ ምስጢራዊነቱ እና ደኅንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን የሴቶችና የሕፃናት የጥቃት ጉዳዮች የሚታዩባቸው ችሎቶች እንደ ሌሎች የወንጀል ችሎቶች ለሕዝብ ክፍት ሳይሆኑ እንደአስፈላጊነቱ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በዝግ ሊካሄዱ እንደሚገባ የሲዳው ኮሚቴ ምክረ ሐሳብ ቁጥር 33 ያብራራል፡፡ ይህን ተግባራዊ ማድረግ የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት ከተጠርጣሪው ሰው እንዲሁም ማኅበረሰቡን ጨምሮ ከሌላ ሦስተኛ ወገን ሊደርስ ከሚችል ሁለተኛ ደረጃ ጥቃት፣ ዳግም ጥቃት እና አድሎአዊ መገለል የሚጠብቅ ከመሆኑም በላይ[17] በፍትሕ ሥርዓቱ እምነት ኖሯቸው ጉዳያቸውን እስከ መጨረሻው እንዲከታተሉ ያግዛቸዋል፡፡[18]

## 2.1.4 የደኅንነት ጥበቃ የማግኘት መብት

የጥቃት ተጎጂ ሴቶች ከአቤቱታ ማቅረብ ጀምሮ በፍትሕ ሥርዓቱ በሚያልፉበት ጊዜ ጥቃት በማድረስ ከተጠረጠረው ሰው፣ ከማኅበረሰቡ ወይም ከማንኛውም ሦስተኛ ወገን ከሚመጣ የሥነ ልቦና ወይም የአካል ጥቃት የመጠበቅ መብት አላቸው፡፡ በመሆኑም ሀገራት ሴት የጥቃት ተጎጂዎችን ስለጥቃቱ ከማመልከታቸው በፊት፣ በፍትሕ ሂደት እያሉ እና የፍትሕ ሂደቱም

[14] The Beijing platform for action (1995)
[15] CEDAW 33, paragraph 51
[16] CEDAW 33, paragraph 33(18(f))
[17] CEDAW 33, paragraph 51
[18] Handbook for Legislation on Violence against Women, prepared by the UN, Department of Economic and Social Affairs/Division for the Advancement of Women (DESA/DAW) July 2009

ከተጠናቀቀ በኂላ ከዛቻ፣ ከትንኮሳ ወይም ከማንኛውም ጉዳት የመጠበቅ ግዴታ እንዳለባቸው እና ውጤታማ የደኅንነት ጥበቃ ለማስፈን አስፈላጊውን የበጀት እና የግብአት አቅርቦት የማቅረብ፣ ለደኅንነት ጥበቃው የሥርዓት መመሪያ እና የሕግ ማዕቀፍ የማዘጋጀት ኃላፊነት እንዳለባቸው በሲዳው ኮሚቴ ምክረ ሐሳብ ቁጥር 33 አንቀጽ 18(ቀ) ተገልጿል፡፡[19]

በተመሳሳይም የጥቃት ተጎጂ ሕፃናት በፍትሕ ሥርዓቱ በሚያልፉበት ጊዜ ከተጠርጣሪው ሰው፣ ከማኅበረሰቡ ወይም ከማንኛውም ሦስተኛ ወገን ከሚመጣ የሥነ ልቦና ወይም የአካል ጥቃት ሊጠበቁ እንደሚገባ የወንጀል ተጎጂ ሕፃናት እና ሕፃናት ምስክሮች የተሳተፉበት ፍትሕ ጉዳዮች መመሪያ[20] እና የሕፃናት መብቶች ስምምነት በሕፃናት ሽያጭ፤ ሕፃናትን ለወሲብ ንግድ ማሰማራት እና የወሲብ ፊልም ማሠራትን ለማስወገድ የተደረገ አማራጭ ፕሮቶኮል በአንቀጽ 8(1) ይደነግጋል፡፡ የወንጀል ተጎጂ ሕፃናት እና ሕፃናት ምስክሮች የተሳተፉበት ፍትሕ ጉዳዮች መመሪያ ሕፃናትን ከጥቃት አድራሹ ተጠርጣሪ በፍትሕ ሂደት ሲያልፉ በቀጥታ እንዳይገናኙ ማድረግ፣ ፍርድ ቤቶች የደኅንነት ጥበቃ ትዕዛዝ እንዲሰጡ ማድረግ፣ ክስ ከመመስረቱ በፊት ወይም በፍርድ ቤት ጊዜ ቀጠሮ ወቅት ተጠርጣሪውን እንደአስፈላጊነቱ መጠን በእስር እንዲቆይ ማድረግ እንዲሁም ተጎጂ ሕፃናትን የደኅንነት ጥበቃ አገልግሎት ለሚሰጡ ተቋማት ጥበቃ ስር እንዲቆዩ ማድረግ እንደ አማራጭ ያስቀምጣሉ፡፡[21] የወንጀል እና ሥልጣንን አላግባብ የመጠቀም ተጎጂ ለሆኑ ሰዎች የወጣው የፍትሕ መሠረታዊ መርሖች መግለጫ[22] ሀገራት ተጎጂ ሕፃናትን ከሦስተኛ ወገን ከሚሰነዘር በቀል እና ማስፈራሪያ ለመጠበቅ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ እንዳለባቸው በአንቀጽ 6(መ) ይደነግጋል፡፡

ሀገራትም የተጎጂ ሕፃናት የደኅንነት ሥጋቶች አግባብ ለሆኑ ተቋማት የሚደርሱበትን ሥርዓት እንዲዘረጉ እንዲሁም ተጎጂዎች በፍትሕ ሥርዓት በሚያልፉበት ጊዜ እና የፍትሕ ሂደቱም ከተጠናቀቀ በኃላ ከደኅንነት ሥጋት ለመጠበቅ አግባብ የሆኑ እርምጃዎችን እንዲወስዱ የወንጀል ተጎጂ ሕፃናት እና ሕፃናት ምስክሮች የተሳተፉበት ፍትሕ ጉዳዮች መመሪያ በአንቀጽ 32 ይመክራል፡፡ የደኅንነት ጥበቃን ማረጋገጥ ተጎጂ ሴቶች እና ሕፃናት በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ውጤታማ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ከማገዙም በላይ የጥቃት አድራሾችን ተጠያቂነት ለማረጋገጥ ትልቅ ሚና ይኖረዋል፡፡ በተለይም ጥቃት አድራሹ የቤተሰብ አባል፣ ዘመድ ወይም በመኖሪያ አካባቢ የሚገኝ ሰው በሚሆንበት ጊዜ የደኅንነት ጥበቃው እጅጉን አስፈላጊ ይሆናል፡፡

### 2.1.5 የመሰማት/ የመሳተፍ መብት

ተጎጂዎች በፍትሕ ሥርዓቱ በሚያልፉበት ጊዜ በሚመለከታቸው ጉዳይ ሁሉ ሐሳባቸውን እና ሥጋታቸውን እንዲያስረዱ ዕድል ሊሰጣቸውና ሐሳቦቻቸውና ሥጋቶቻቸው በሚወሰኑት

[19] CEDAW 33, Paragraph 18(g)

[20] UN Economic and Social council resolution: Guidelines on justice in matters involving child victims and witess of crime, 2005 (hereinafter referred to as 'Guidelines on justice in matters involving child victims') Article 32-34

[21] Guidelines on justice in matters involving child victims Article 34

[22] Declaration of Basic principles of justice for victims of crime and abuse of power

ውሳኔዎች ታሳቢ ሊደረጉ እንደሚገባ የወንጀል እና ሥልጣንን አላግባብ የመጠቀም ተጎጂ ለሆኑ ሰዎች የወጣው የተባበሩት መንግሥታት የፍትሕ መሠረታዊ መርሖች መግለጫ በአንቀጽ 6(ለ) ይደነግጋል።[23] ይህን ተግባራዊ ማድረግ የፍትሕ ሥርዓቱ ምላሽ አሰጣጥ የተጎጂዎችን ፍላጎት ያማከለ እንዲሆን ያግዘዋል። በተመሳሳይ ሐሳቡን የመግለጽ ችሎታ ያለው ማንኛውም ሕፃን በሚመለከተው ጉዳይ ሁሉ ሐሳቡን በነጻነት የመግለጽ መብት እንዳለውና ሀገራትም ይህንን መብት መተግበሩን እንዲያረጋግጡ የሕፃናት መብቶች ስምምነት በአንቀጽ 12 ይደነጋጋል። ሕፃናትን የተመለከቱ ጉዳዮች በዳኝነት ወይም በአስተዳደር አካል በሚታዩበት ጊዜ ሕፃናት ራሳቸው በቀጥታ ወይም በእንደራሴ ወይም አግባብነት ባለው አካል በኩል የመሰማት ዕድል ሊሰጣቸውና የሚያቀርቧቸውም ሐሳቦች ዕድሜያቸውና የአእምሮ የእድገት ሁኔታቸው እየታየ ተገቢው ክብደት ሊሰጣቸው እንደሚገባ የሕፃናት መብቶች ስምምነት በአንቀጽ 12(1) እና (2) ይደነግጋል። ሕፃናት ሐሳቦቻቸውን፣ ምርጫዎቻቸውንና ፍላጎቶቻቸውን ለመግለጽ የሚጠቀሟቸውን እንደ ፊት ገጽታ፣ የሰውነት ምልክቶች፣ በስዕል እና በቀለማት የሚገለጹ ሐሳቦቻቸውን ዕውቅና ሊሰጧቸውና በመሰል ክንውኖች የገለጹዋቸው ሐሳቦችም ሊከበሩላቸው እንደሚገባ የሕፃናት መብቶች ስምምነት ትንታኔ ያስረዳል። ሕፃናት ሐሳባቸው በራሳቸው ላይ ስለሚኖረው ውጤት ዝርዝር ዕውቀት እንዲኖራቸው ሳይጠበቅ የመሰማት መብታቸው ሊጠበቅ ይገባል። ሀገራት በመደበኛ ሁኔታ ሐሳባቸውን መግለጽ ለሚቸገሩ ሕፃናትም በተለይም ለአካል ጉዳተኛ ሕፃናት ሐሳባቸውን እንዲገልጹ የሚያስችሉ አስፈላጊ እገዛዎችና መገልገያዎች ሊሟሉላቸው ይገባል።[24]

በተጨማሪም ሀገራት የሕፃናትን የመሰማት መብት ለማረጋገጥ ሕፃናት የሚገኙባቸው ክፍሎች የሕፃናትን ፍላጎት እና የዕድሜ ሁኔታ ያገናዘበ እንዲሁም የሚያስተናግዷቸው ባለሙያዎችም በሕፃናት ፍላጎት/መብቶች ላይ የሰለጠኑ እንዲሆኑ ይገደዳሉ።[25] ይህም ማለት ሕፃናት የሚስተናገዱባቸው ክፍሎች እና አሠራሮች ለሕፃናት ፍርሀት እና የስሜት መረበሽን የማይፈጥሩ እንዲሁም ነጻ ሆነው ሐሳባቸውን መግለጽ የሚያስችሉ ሊሆኑ ይገባል። ስለጥቃቱ የክስ ሁኔታ፣ የምርመራ ሂደት፣ ስለተጠርጣሪው በቁጥጥር ስር መዋል፣ በጊዜ ቀጠሮ ስለሚኖር ዋስትና (በተጎጂ ደኅንነት ላይ ስለሚኖረው ተጽዕኖ) እንዲሁም በክስ መዝገቡ የሚወሰኑ ማናቸውም ውሳኔዎች የተጎጂ ሴቶችና ሕፃናትን መብቶች ሊነኩ የሚችሉ በመሆናቸው እነዚህን ጉዳዮች አስመልክቶ ተጎጂዎችን ማሳወቅ እና ሐሳቦቻቸውን እንዲያሰሙ ዕድል መስጠት ይገባል።

[23] Basic principles of justice for victims of crime and abuse of power
[24] UN Committee on the Rights of the Child (CRC), General comment No. 12 (2009): The right of the child to be heard, 20 July 2009
[25] UN Committee on the Rights of the Child (CRC), General comment No. 12 (2009): The right of the child to be heard 20 July 2009

### 2.1.6 የተፋጠነ ፍትሕ እና ውጤታማ መፍትሔ የማግኘት መብት

የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት የተፋጠነ ፍትሕ የማግኘት መብት አላቸው፡፡ በፍትሕ አካላት የሚታዩ የጥቃት ክስ ጉዳዮች በተፋጠነ ሁኔታ ወይም አግባብ በሆነ የጊዜ ገደብ ውሳኔ ሊሰጥባቸው ይገባል፡፡ የሲዳው ኮሚቴ ምክረ ሐሳብ ቁጥር 33 በአንቀጽ 51 (ተ)፣ 19(ሀ)፣ 19(ሰ)፣ 14(መ) እና በ 18(መ) እንዲሁም በተለያዩ የምክረ ሐሳቡ አንቀጾች ሀገራት የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት የተፋጠነ ፍትሕ የማግኘት መብታቸውን የማረጋገጥ ግዴታ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡

የሕፃናት መብቶች ስምምነት በሕፃናት ሽያጭ፣ ሕፃናትን ለወሲብ ንግድ ማሰማራት እና የወሲብ ፊልም ማሠራትን ለማስወገድ የተደረገ አማራጭ ፕሮቶኮል[26] የሕፃናት ጉዳዮች አላስፈጊ መዘግየቶች ሳይኖሩ በፍጥነት እንዲያልቁ እና የተሰጡት የካሳ ትዕዛዞች ወይም ውሳኔዎች በፍጥነት እንዲፈጸሙ እንዲሁም ሕፃናት በሕግ ካሳ እንዲሰጥ ኃላፊነት ከተጣለበት ሰው ያለ ምንም አድልዎ ካሳ የሚያገኙበት በቂ የሆነ አሠራሮች ሊኖራቸው እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡ የጥቃት አቤቱታ ወደ ፍትሕ አካላት ከደረሰ በኋላ አቤቱታ የደረሰው የፖሊስ አባል በአጭር ጊዜ ውስጥ ወይም አግባብ በሆነ የጊዜ ገደብ ጉዳዩን በቀጣይ ለሚመለከተው የመርማሪ ፖሊስ ማስተላለፍ ይኖርበታል፡፡ ምርመራውን የማከናወን ኃላፊነት የተሰጠው አካል ምርመራውን አጠናቆ እንደሁኔታው አቤቱታው/ክሱ ለችሎት እንዲቀርብ ወይም በደረሰው መዝገብ ላይ ውሳኔ ማስተላለፍ ይኖርበታል፡፡ በተመሳሳይም ጉዳዩ የደረሰው የችሎት ዳኛ በመዝገቡ ላይ በተፋጠነ ወይም አግባብ በሆነ የጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ ውሳኔ እንዲያስተላልፍ ይጠበቃል፡፡ የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት የተፋጠነ ፍትሕ የማግኘት መብታቸውን መተግበር ተጎጂዎችን ከሁለተኛ ደረጃ እና ከዳግም ጥቃት በመጠበቅ ረገድ የጎላ ሚና ይኖረዋል፡፡

ውሳኔዎች ፈጣን ብቻ ሳይሆን ለተጎጂው ውጤታማ መፍትሔ የሚሰጡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ሀገራት ሴቶችን ከጾታዊ ጥቃት ለመጠበቅ መውሰድ ከሚጠበቅባቸው እርምጃዎች አንዱ የሕግ እርምጃዎች ሲሆኑ ይህም የወንጀል ቅጣት፣ የፍትሐ ብሔር መፍትሔ እንዲሁም ካሳን የተመለከቱ ድንጋጌዎች በሕጎቻቸው ማካተት እንደሆነ የሲዳው ኮሚቴ ልዩ ምክረ ሐሳብ አንቀጽ 24(0) ያትታል፡፡[27] ውጤታማ የሕግ መፍትሔ ተፈጻሚ እንዲሆን ደግሞ የፍትሕ ተቋማት ማለትም ፖሊስ፣ ዐቃቤያነ ሕግ እና ዳኞች በትጋት ኃላፊነታቸውን የመወጣት ግዴታ እንዳለባቸው በሲዳው ኮሚቴ ምክረ ሐሳብ ቁጥር 33 በአንቀጽ 51(ሀ)፣ ሸ እና (ተ) ላይ ተጠቅሷል፡፡ በፍትሕ ሥርዓቱ ለተጎጂው የሚኖረው አንደኛው ውጤታማ የሕግ መፍትሔ የጥቃት አድራሹን ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ነው፡፡ የጥቃት አድራሹ ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ ደግሞ ፖሊስ አና ዐቃቤ ሕግ በሴቶች እና በሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን በአማራጭ ግጭት መፍቻ ከመፍታት በመታቀብ[28]

---

[26] Optional protocol to the convention on the sale of children, child prostitution and child pornography 2002, article 8(1)

[27] CEDAW 19

[28]የኮሚቴው አጠቃላይ ምክረ ሐሳብ ቁ. 35 አስቀድሞ በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃትን አስመልክቶ የተሰጠውን አጠቃላይ ምክረ ሐሳብ 19 ለማሻሻል በተመሳሳይ ርዕሠ ጉዳይ ላይ የተሰጠ ምክረ ሐሳብ እንደመሆኑ የጾታዊ ጥቃትን አስመልክቶ በአማራጭ የግጭት መፍቻ ሊታይ ሚችልበትን ጥብቅ ቅድመ ሁኔታዎችን በአንቀጽ 32(ለ) አስቀምጧል ፡፡

በትጋት ምርመራ እንዲያካሂዱ እና ጥቃት አድራሹን ተገቢውን ቅጣት እንዲያስቀጡ የአፍሪካ የሴቶች መብቶች ፕሮቶኮል (የማፑቶ ፕሮቶኮል) በአንቀጽ 4 (2) (ሠ)፣ (ሸ) እንዲሁም በሲዳው ኮሚቴ ምክረ ሐሳብ ቁጥር 19 አንቀጽ 9 ተገልጿል፡፡[29]

በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ተጎጂዋ አንደ ፍትሐ ብሔር ክርክር ከሳሽ ባለመሆኗ ለጉዳዩ ማስረጃ የመሰብሰብ እና የተጠርጣሪውን ተጠያቂነት ማረጋገጥ የዐቃቤ ሕግ እና የመርማሪ ፖሊስ የሥራ ድርሻ ይሆናል፡፡ ፖሊስ እና ዐቃቤ ሕግ የተጠርጣሪውን ተጠያቂነት ለማረጋገጥ የተጎጂዋን ቃል ብቻ መሠረት ከማድረግ ይልቅ በራሳቸው ትጋት እና ጥረት በቂ ማስረጃዎችን በማሰባሰብ ጥቃት አድራሹን ተጠያቂ እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡ ይህን ተግባራዊ ማድረግም በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን የመቀነስ እና ፍትሐዊ እና ውጤታማ ምላሽ የመስጠት ማሳያ ይሆናል፡፡[30] የሲዳው ኮሚቴ ምክረ ሐሳብ ቁጥር 33 አንቀጽ 51(ሸ)[31] ሀገራት በማስረጃ ሕጎቻቸው የወንጀሉ ልዩ ጠባይ ከግምት በማስገባትና ሚዛናዊነትን በማስጠበቅ እጅግ ጥብቅ ያልሆኑ የማስረጃ ደንቦችን እንዲተገብሩ ያሳስባል፡፡ ይህም ማለት የወንጀሉ ዐይነት በሴቶችና ሕፃናት ላይ የተፈጸመ ጥቃት በሚሆንበት ጊዜ ለማስረጃነት የሚቀበሏቸው ማስረጃዎች እንደሌላ የወንጀል ዐይነት እጅግ ጥብቅ እንዲሆኑ ሳያስፈልግ ወንጀሉ ስለመፈጸሙ በቀጥታ ሊያሳዩ የማይችሉ አካባቢያዊ ማስረጃዎች ተቀባይነት እንዲኖራቸው የሚያስችል ነው፡፡

ጥቃት አድራሹን ተጠያቂ ከማድረግ በተጨማሪ ተጎጂዎች በደረሰባቸው ጉዳት ልክ ፈጣን የሆነ የገንዘብ ካሳ እና የማገገሚያ አገልግሎት የማግኘት መብት እንዳላቸው እና ሀገራት ይህንን መብት የመተግበር ግዴታ እንዳለባቸው የሲዳው ኮሚቴ ምክረ ሐሳብ ቁጥር 35 አንቀጽ 33 ይገልጻል፡፡ የማገገሚያ አገልግሎት ተጎጂዎች ከደረሰባቸው ጉዳት በተቻለ መጠን በተሟላ መልኩ እንዲያገግሙ የሚረዱ የጤና፣ የሥነ ልቦና እና የማኅበራዊ አገልግሎቶችን ይጨምራል፡፡ በተመሳሳይም ሕፃናት የጥቃት ተጎጂዎች ፍትሐዊ እና በቂ ካሳ እንዲያገኙ ሊደረግ እንደሚገባ የወንጀል ተጎጂ ሕፃናት እና ሕፃናት ምስክሮች የተሳተፉበት ፍትሕ ጉዳዮች መመሪያ ይመክራል፡፡[32]

---

29 Maputo Protocol, article 19, 4.2 e and f; CEDAW 19, paragraph 24 i and Paragraph 9; CEDAW 33 paragraph 58; Report of the Fourth World Conference on Women, Beijing, 4 -15 September 1995 (United Nations publication, Sales No. E.96.IV.13)

30 CEDAW 19, paragraph 24 I, g and s

31 51. **The Committee recommends that States parties:**(h) **Review rules of evidence and their implementation, especially in cases of violence against women, and adopt measures with due regard to the fair trial rights of victims and defendants in criminal proceedings, to ensure that the evidentiary requirements are not overly restrictive, inflexible or influenced by gender stereotypes.**

32 Guidelines for Action on Children in the Criminal Justice System, Economic and Social Council resolution 1997/30, 1997, Article 48

## 2.1.7 የድጋፍ አገልግሎት የማግኘት መብት

የጥቃት ተጎጂ ሴቶች እና ሕፃናት በፍትሕ ሥርዓቱ በሚያልፉበት ጊዜ እና የፍትሕ ሂደቱም ከተጠናቀቀ በኋላ አስፈላጊውን የሕክምና፣ የሥነ ልቦና፣ የመጠለያ፣ የማገገሚያ እና የሕግ ድጋፍ የማግኘት መብቶች አሏቸው። ሀገራትም እነዚህን ድጋፍ የማግኘት መብቶችን ዕውቅና እንዲሰጡ እና በሕጎቻቸውም እንዲያካትቱ የሲዳው ኮሚቴ ምክረ ሐሳብ 33 በአንቀጽ 15(ሀ) እና በሲዳው ኮሚቴ ምክረ ሐሳብ ቁጥር 19 በአንቀጽ 24(ለ) ተገልጿል።
የሕግ ድጋፍን በተመለከተ ሀገራት ለሴቶች ጥቃት ምላሽ የሚሰጥ እና አገልግሎቶቹ ፈጣን እና ውጤታማ የሆነ የሕግ ድጋፍ ተቋማዊ እንዲያደርጉ የሲዳው ኮሚቴ ምክረ ሐሳብ ቁጥር 33 አንቀጽ 37 ያብራራል። ነጻ የሕግ ድጋፍ ወይም በአነስተኛ የገንዘብ መጠን የሚሰጥ የሕግ ድጋፍ ለሴቶች የኢኮኖሚ ዐቅምን መሠረት ያደረገ (economically accessible) የፍትሕ ሥርዓት ለማረጋገጥ ቁልፍ ሚና አለው።[33]

ከሕግ ድጋፍ በተጨማሪ የገንዘብ እርዳታ፣ የመጠለያ አገልግሎት፣ ነጻ የስልክ ጥሪ አገልግሎቶች፣ የሕክምና እና የሥነ ልቦና ሕክምና፣ የምክር አገልግሎቶች እንዲሁም የመጠለያ አገልግሎቶችን ሀገራት የማቅረብ ግዴታ እንዳለባቸው የሲዳው ኮሚቴ ምክረ ሐሳብ ቁጥር 33 አንቀጽ 16(ለ) እና (ሐ)ይገልጻል። በተመሳሳይም የአፍሪካ የሴቶች መብቶች ፕሮቶኮል (የማፑቶ ፕሮቶኮል በአንቀጽ 4(2) (ሰ) ሀገራት ለጥቃት ተጎጂ ሴቶች ተደራሽ የሆነ የማገገሚያ አገልግሎት መርኃ ግብሮችን ለመተግበር አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ እንደሚገባቸው ይደነግጋል። የሕፃናት መብቶች ስምምነትም እንዲሁ ተጎጂ ሕፃናት በአካልና በሥነ ልቦና ከደረሰባቸው ጉዳት እንዲያገግሙና ከኅብረተሰቡ ጋር መልሰው እንዲቀላቀሉ የስምምነቱ ፈራሚ ሀገራት ተገቢውን እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸው ይደነግጋል።[34]

## 2.2 የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ያላቸው መብቶች በኢትዮጵያ የሕግ ማዕቀፍ

## 2.2.1 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢ.ፌ.ዴ.ሪ.) ሕገ-መንግሥት

የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት፣ አንቀጽ 35(4) በሴቶች አካል ወይም አእምሮ ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ልማዶች የተከለከሉ መሆናቸውን እንዲሁም በአንቀጽ 36(1) ሕፃናት በጤናና ደኅንነታቸው ላይ ጉዳትን ከሚያስከትሉ ልማዶች የመጠበቅ መብት እንዳላቸው ይደነግጋል። በሕገ መንግሥቱ በአንቀጽ 37 (1) ማንኛውም ሰው ፍትሕ የማግኘት መብትን በተመለከተ በፍርድ ሊወሰን የሚችል ጉዳይን ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለው ይደነግጋል። ከላይ የተዘረዘሩት ድንጋጌዎች የሚገኙበት የሕገ መንግሥቱ የመሠረታዊ መብቶች እና ነጻነቶች ምዕራፍ አተረጓጎም ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግጋት፣ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች እና ዓለም አቀፍ ሰነዶች መርሆች ጋር በተጣጣመ መንገድ እንደሚተረጎም

[33] CEDAW 33, paragraph 3
[34] CRC, Article 39

በዚሁ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 13(2) ተደንግጓል፡፡ ይህም ማለት የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት በሚያልፉበት ጊዜ ፍትሕ የማግኘት መብታቸው ከዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ፣ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች እና ሰነዶች መርሖች ጋር የተጣጣመ ሊሆን እንደሚገባው አና መንግሥትም በእነዚህ መርሖች የተቀመጡትን መብቶች በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓትም ተፈጻሚ የማድረግ ኃላፊነት አለበት ማለት ነው፡፡

## 2.2.2 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የተካተቱትን እና ለወንጀል ፍትሕ ሥርዓት አግባብነት ያላቸውን መርሖች፣ ድንጋጌዎች እና ዕሴቶች፣ እንዲሁም በሕገ መንግሥቱ መሠረት የኢትዮጵያ የሕግ አካል የሆኑ ዓለም አቀፍ ሕጎች፣ ስምምነቶችና ሠነዶችን መሠረት አድርገው እንደሚፈጸሙ ይደነግጋል፡፡ ይህ ፖሊሲ በወንጀል ጉዳት የደረሰበት ሰው በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ሊኖሩት ስለሚገቡ መብቶች፣ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎችን እና ስምምነቶችን መለኪያ አድርጎ ዕውቅና ከመስጠት በተጨማሪ፤ የወንጀል ተጎጂ ለሆነ ማንኛውም ሰው በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የወንጀል ፍትሕ አሠራር እንደሚዘረጋ እና ለአፈጻጸሙም የተለያዩ እርምጃዎች እንደሚወሰዱ ይገልጻል፡፡

ፖሊሲው ተጎጂዎች በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ሲያልፉ የመሳተፍ እና መረጃ የማግኘት፣ የድጋፍ አገልግሎት የማግኘት፣ ምስጢራዊነቱ እና ደኅንነቱ የተጠበቀ የፍትሕ አገልግሎት የማግኘት፣ የሕፃናትን ጥቅም እና ፍላጎት ያስቀደመ የፍትሕ አገልግሎት የማግኘት፣ ውጤታማ እና አፋጣኝ መፍትሔ የማግኘት እና በፍትሕ ሥርዓቱ በክብር የመስተናገድ መብቶችን ዕውቅና ይሰጣል፡፡ ጾታን መሠረት ካደረገ ጥቃት ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮችም አማራጭ የመፍትሔ እርምጃዎች ሊወሰዱ እንደማይገባ ያትታል፡፡

ፖሊሲው ከላይ የተጠቀሱትንና ተያያዥ መብቶችን ለመተግበር የሁሉንም የወንጀል ተጎጂዎች መብቶች ማስከበር በሚያስችል መልኩ የወንጀል እና የሥነ ሥርዓት ሕጎችን ማሻሻል፣ ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃትን ጨምሮ በወንጀል ድርጊት ተጎጂ የሆኑ ሴቶችን የተለየ አያያዝ የሚመለከቱ ግልጽ የሕግ ድንጋጌዎችን በሕጎች ውስጥ ማካተት፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሕግ አስፈጻሚ እና የፍትሕ አካላት በወንጀል ጉዳት ከደረሰባቸው ሕፃናት ጋር በተያያዘ ስለሚያከናውኗቸው ተግባራት እና ስለሚወስዷቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣ የወንጀል ምርመራ የሚጠናቀቅበትን እና በጉዳዩ ላይ ክስ ማቅረብ የሚቻልበትን የጊዜ ገደብ በተመለከተ መመሪያዎችን ማውጣት እንዲሁም በወንጀል ድርጊት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ለደረሰው ጉዳት በፍርድ ቤት ወይም በሌሎች አማራጭ ዘዴዎች የካሣ ጥያቄ በማቅረብ ተገቢውን ካሣ በአፋጣኝ እንዲያገኙ ማድረግ የሚያስችሉ አመቺ የአሠራር ሥርዓቶችን መዘርጋት የሚሉትን እንደመፍትሔ አስቀምጧል፡፡

### 2.2.3 የኢትዮጵያ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ

ፍትሕ የማግኘት መብት በሕገ መንግሥቱ መሠረት ከዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግጋት መርሖዎች እና ድንጋጌዎች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ የሚተረጎም ቢሆንም፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ የጥቃት ተጎጂዎችን መብቶች በተመለከተ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግጋትን እንደ መለኪያ ዕውቅና ቢሰጥም፣ አሁን በሥራ ላይ ያለው የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ የሚሸፍነው እጅግ ውስን የሆኑ የተጎጂዎች መብቶችን ነው፡፡ የሥነ ሥርዓት ሕጉ የጥቃት ተጎጂ ሴቶችን እና ሕፃናትን አስመልክቶ በቅድመ-ክስ፣ በክስ መስማት እና ድኅረ-ክስ ሂደቶች የተለየ የመብቶች አያያዝ አላስቀመጠም፡፡ ስለሆነም የጥቃት ተጎጂ ሴቶች እና ሕፃናት የሚኖሯቸው መብቶች እንደማንኛውም የወንጀል ድርጊት ተጎጂ የግል ክስ የማቅረብ መብት፣ ለበላይ ዐቃቤ ሕግ አቤቱታ የማቅረብ መብት፣ ምስክርነት የመስጠት መብት እና በግል ክስ ይግባኝ የማቅረብ መብቶች ናቸው፡፡

#### 2.2.3.1 የግል ክስ የማቅረብ መብት

ዐቃቤ ሕግ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ (ወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ) አንቀጽ 42(1))ሀ) መሠረት ጥፋተኛ ለማድረግ በቂ የሆነ መረጃ የሌለ መሆኑን ከተረዳ እና ይህም ውሳኔ የተሰጠበት መዝገብ በግል-አቤቱታ አቅራቢነት የሚያስቀጣ ወንጀል[35] በሆነ ጊዜ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 44(1) እና 47 መሠረት ዐቃቤ ሕጉ ለተገቢው የግል ክስ አቅራቢ የግል ክስ እንዲያቀርብ በጽሑፍ ይፈቅድለታል፡፡ በዚሁ ሕግ አንቀጽ 43 (1) እና (2) መሠረት ዐቃቤ ሕግ የክስ አይቀርብም ውሳኔውን እና የውሳኔውን ምክንያት በጽሑፍ የግል ክሥ የማቅረብ መብት ለተሰጠው ሰው ወይም ለእንደራሴው ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

#### 2.2.3.2 ለበላይ ዐቃቤ ሕግ አቤቱታ የማቅረብ መብት

በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 42 (1)(ሀ) መሠረት የክስ አይመሰረትም ውሳኔ የተሰጠበት መዝገብ የክስ አቤቱታ ማቅረብ ሳያስፈልግ የሚያስቀጣ ወንጀል በሆነ ጊዜ የወንጀል ተጎጂዎች በዚሁ የዐቃቤ ሕግ ውሳኔ ቅር ከተሰኙ በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀጽ 18 መሠረት አቤቱታቸውን ለበላይ ዐቃቤ ሕግ ማቅረብ የሚችሉ ሆኖ፣ እነኝህን ዐይነት ወንጀሎች በተመለከተ የወንጀል ተበዳዮች ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የግል-ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም፡፡ ከዚህ በተለየ በወንጀል ተጎጂ የሆኑ ሰዎች በተከሳሹ የዋስትና መብት እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ አስተያየት እና ቅሬታ የማቅረብ መብት ያልተሰጣቸው መሆኑ የመሰማት መብታቸውን የሚያጣብብ ነው፡፡

---

[35] በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ወይም በሌላ ማሟያ የወንጀል ሕግ ከግል ተበዳይ ወይም ሕጋዊ ወኪል አቤቱታ ውጭ የወንጀል ክስ የማይቀርብባቸው ተብለው የተደነገጉ የወንጀል ዐይነቶችን ይመለከታል፡፡ (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 212) ፡፡ በግል አቤቱታ አቅራቢነት የሚያስቀጡ ወንጀሎች በባህሪያቸው ጉዳታቸው ቀላል እና ከግል ተበዳይ ባለፈ በሕዝብና በሀገር ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ አይደሉም፡፡ ስድብ፣ ስም ማጥፋት፣ ዛቻ እና መሰል ድርጊቶች በግል አቤቱታ አቅራቢነት የሚያስቀጡ የወንጀል ዐይነቶች ውስጥ ይካተታሉ፡፡

### 2.2.3.3 የፍትሐ ብሔር ክስ ከወንጀል ክስ ጋር ተጣምሮ በሚቀርብበት ጊዜ ተጎጂዎች የሚኖራቸው መብት

የወንጀል ተጎጂዎች በደረሰባቸው ጉዳት ካሳ መጠየቅ እንዲችሉ የፍትሐ ብሔር ክስ ከወንጀል ክስ ጋር ተጣምሮ እንዲቀርብ የሚያስችል ድንጋጌ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 101 እና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 155 ይገኛል። ከወንጀል ክስ ጋር የተጣመረው የፍትሐ ብሔር ክስ በዐቃቤ ሕግ በኩል የቀረበ ከሆነ እና ፍርድ ቤቱ ማመልከቻውን ያልተቀበለው እንደሆነ የወንጀል ተጎጂው ይህንኑ የፍትሐ ብሔር ክስ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ማቅረብ የሚችል ቢሆንም፣ በወንጀል ጉዳዩ ያለው ተሳትፎ ግን ምስክርነት መስጠት ላይ ብቻ የተገደበ ነው። በአጠቃላይ በወንጀል ምክንያት የደረሰን ጉዳት በተመለከተ የፍትሐ ብሔር ክስ ከወንጀል ክስ ጋር ተጣምሮ መቅረቡ የወንጀል ተጎጂ የሆኑ ሰዎች በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ የሚያሳይ ቢሆንም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 155 የፍትሐ ብሔር ክሱ ውድቅ ሊደረግባቸው የሚችሉባቸው ምክንያቶች በርካታ እንደሆኑ ያሳያል።

### 2.2.3.4 ይግባኝ የማቅረብ መብት

በድኅረ-ፍርድ ሂደቶች ላይ የወንጀል ተጎጂ የሆኑ ሰዎች ያላቸውን ተሳትፎ በተመለከተ የሚነሳው ሌላው ጉዳይ ይግባኝ የማቅረብ መብት ነው። የወንጀል ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ሲመለከተው የነበረው ፍርድ ቤት በመዝገቡ ላይ ፍርድ ካስተላለፈ በኃላ፣ በፍርዱ ቅር የተሰኘ አካል ይግባኝ የማቅረብ መብት እንዳለው መነገር እንዳለበት የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 149(7) ተቀምጧል።

ይህ ይግባኝ የማቅረብ መብት የግል-ክስ የቀረበባቸው መዝገቦችንም የሚያጠቃልል በመሆኑ የወንጀል ተጎጂዎች በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካላቸው ይግባኝ የማቅረብ መብት አላቸው። ከወንጀል ክስ ተጣምሮ የቀረበ የፍትሐ ብሔር ክስ ካለም ፍርድ ቤቱ የወሰነውን የጉዳት ካሳ መጠን በተመለከተም ይግባኝ ሊቀርብበት እንደሚችል የ/ወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 186 ድንጋጌ ያሳያል። ሆኖም ግን የወንጀል ጉዳዮች በወንጀል ክስ አቅራቢነት የሚያስቀጣ በሆነ ጊዜ የወንጀል ተጠያቂነትን በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠን ውሳኔ አስመልክቶ ይግባኝ የማቅረብ መብት ያለው ዐቃቤ ሕግ ብቻ በመሆኑ የወንጀል ተጎጂዎች የሚያደርጉት ተሳትፎ የለም።

### 2.2.3.5 በፍርድ ቤቶች የተፋጠነ ፍትሕ የማግኘት መብት

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 በአንቀጽ 19 (ሰ) "የየፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንቶች ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት የተፈጸመባቸው ሴቶች፣ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያንን አስመልክቶ በፍርድ ቤቶች የሚከፈቱ መዝገቦች በተፋጠነ ፍትሕ አገልግሎት እልባት እንዲያገኙ እና የሕግ ባለሙያ ድጋፍ እንዲሰጣቸው ያደርጋሉ" ሲል ይደነግጋል። የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በሴቶች እና በሕፃናት የሚፈጸሙ ጉዳዮች በተፋጠነ ሥነ ሥርዓት እልባት የማግኘት መብት የሕግ መሠረት እንዲኖረው ያስችላል።

# ክፍል ሦስት

# ዋና ዋና ግኝቶች

## 3.1 ፍትሕ የማግኘት መብት

የፍትሕ ተደራሽነት የፍትሕ እና የድጋፍ ሰጪ ተቋማት ኢኮኖሚያዊ ተደራሽነትን (economic accessibility) ፣ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ መሆንን፣ የቋንቋ እና የመረጃ ተደራሽነትን ይጨምራል። ኢኮኖሚያዊ ተደራሽነት የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ለሁሉም ማኅበረሰብ በቅርበት የሚገኙ ወይም የተቋማትን አገልግሎት ለማግኘት የጊዜ እና የመጓጓዣ ወጪ የማያስወጡ ወይም የጊዜ እና የመጓጓዣ ወጪዎች በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚኖሩ የማኅብረተሰብ ክፍሎችን ዐቅም ያገናዘቡ መሆንን ይጨምራል።

በኢትዮጵያ በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀሎችን ከመደበኛው የወንጀል ምላሽ አሰጣጥ በተለየ ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት እንዲሁም ለሕፃናት ፍትሕን ለማረጋገጥ ከሚመለከታቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር በተደረገ መግባባት፣ ለወሲባዊ ጥቃት ተጎጂዎች የተቀናጀ የሕግ፣ የጤና፣ የሥነ ልቦናና ማኅበራዊ አገልግሎት የሚሰጥ የአንድ ማእከል አገልግሎት ከ2001 ዓ.ም. ጀምሮ እንዲቋቋም ተደርጓል።[36] እነዚህ የአንድ ማእከል አገልግሎት ተቋማት የተቋቋሙበትን ዓላማ እንዲያሳኩ የሚያግዝ የሥራ ማስፈጸሚያ መመሪያ በ2003 ዓ.ም. ከዚያም በድጋሚ በ2014 ዓ.ም. የወጣ ሲሆን መመሪያውም አንድ ማእከል መርማሪ ፖሊስ፣ ዐቃቤ ሕግ፣ የጤና ባለሙያ እና የሥነ ልቦና ባለሙያዎችን የያዘ መሆን አለበት ሲል ያትታል።[37]

በተደረገው ክትትል በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የአንድ ማእከል አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት አራት ብቻ ሲሆኑ እነሱም የጋንዲ የተቀናጀ የአንድ ማእከል፣ አበበች ጎበና የተቀናጀ የአንድ ማእከል፣ ጥሩነሽ ቤጂንግ የተቀናጀ የአንድ ማእከል እና የምኒልክ ሆስፒታል የተቀናጀ የአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫዎች ናቸው። እነዚህ ማእከላትም በአዲስ አበባ ከተማ ለሚገኙ አሥራ አንድ ክፍለ ከተሞች እና በአዲስ አበባ ዙሪያ ለሚገኙ አካባቢዎች አገልግሎት የሚሰጡ በመሆናቸው አገልግሎቱን ለማግኘት ከሩቅ አካባቢ ወደ ተቋማቱ ለሚመጡ ተጎጂዎች የመጓጓዣ ወጪ የሚጠይቅ በመሆኑ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ላሉ ተጎጂዎች ኢኮኖሚያዊ ተደራሽነት የሌላቸው ናቸው።

የማዕከሉ ማስፈጸሚያ መመሪያ የተቀናጀ የአንድ ማእከል አገልግሎት ተቋማት መርማሪ ፖሊስ፣ ዐቃቤ ሕግ፣ የጤና እና የሥነ ልቦና ባለሙያዎች በአንድ ጣሪያ የያዙ መሆን እንደሚገባቸው ቢያስቀምጥም በተደረገው ክትትል ስለጥቃቱ መረጃውን የሚያደራጀው ፖሊስ እና ክስ

---

[36] የወሲባዊ ጥቃት ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት የተቀናጀ የአንድ ማዕከል አገልግሎት የአሠራር ሥርዓት ማኑዋል፣ ገጽ 5 እና 6
[37] የወሲባዊ ጥቃት ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት የተቀናጀ የአንድ ማዕከል አገልግሎት የአሠራር ሥርዓት ማኑዋል፣ ገጽ 8

የሚመሰርት ዐቃቤ ሕግ በተቀናጀ የአንድ ማእከል ውስጥ አገልግሎት እንደማይሰጡ እና በሁሉም ማእከሎች የሕክምና እና የሥነልቦና አገልግሎት ብቻ እየሰጡ እንደሚገኙ መረዳት ተችሏል። የአቤቱታ ቅበላ፣ የምርመራ ሥራ፣ የሕክምና እና የሥነልቦና አገልግሎት በአንድ ማእከል የማይሰጥ በመሆኑ ተጎጂዎች ወደ ፖሊስ ጣቢያ፣ ፖሊስ መምሪያ፣ ዐቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤት ለመሄድ እና ለሕክምና አገልግሎቶች ተደጋጋሚ የመጓጓዣ ወጪ እንዲያወጡ ምክንያት በመሆኑ የአቤቱታ ቅበላ፣ የምርመራ ሥራ እና የሕክምና ምርመራ የሚከውኑ የፍትሕ እና የድጋፍ አገልግሎት ተቋማት በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎች ኢኮኖሚያዊ ተደራሽነት እንዳይኖራቸው አድርጓል።

የፍርድ ቤቶችን ኢኮኖሚያዊ ተደራሽነት በተመለከተ በተወሰኑ ምድብ ችሎቶች፣ ችሎቶቹ በሚገኙበት የክፍለ ከተማ ዐቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤት የተከፈቱ የጥቃት ጉዳዮች ብቻ የሚያዩ ሲሆን የተወሰኑ ፍርድ ቤቶች ደግሞ ከተለያየ ምድብ ችሎቶች የመጡ የጥቃት ጉዳዮችን እንደሚያዩ በክትትሉ ታውቋል። በመሆኑም የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት ለምስክርነት ከአካባቢያቸው ርቀት ወዳላቸው ፍርድ ቤቶች የመጓጓዣ ወጪ አውጥተው የሚሄዱ በመሆኑ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎች ኢኮኖሚያዊ ተደራሽነት እንዳይኖራቸው አድርጓል።

በሸገር ከተማ አስተዳደር በቡራዩ ክፍለ ከተማ የሚገኙት የፍትሕ ተቋማት አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ አንድ የዐቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤት እና አንድ የፖሊስ መምሪያ የያዙ ሲሆኑ ተቋማቱ በክፍለ ከተማው ሥር ለሚገኙ አራት ወረዳዎች አገልግሎት ይሰጣሉ። እነዚህ የፍትሕ ተቋማት ለሚገኙበት ወረዳ በአንጻራዊነት ተደራሽ ቢሆኑም ለተቀሩት ሦስት ወረዳዎች ግን የመጓጓዣ ወጪ የሚያስወጡ እና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች ላይ ኢኮኖሚያዊ ተደራሽነታቸው ውስን ነው።

በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን፣ በጅማ ከተማ እና በሸቤ ሶምቦ አዋሳኝ ወረዳ በተደረገው ክትትል የጅማ ዞን ፍርድ ቤት፣ ዐቃቤ ሕግ ቢሮ እና ፖሊስ ጽሕፈት ቤት በዞኑ አስተዳደር ሥር ለሚገኙ 21 ወረዳዎች አገልግሎት የሚሰጡ ሲሆን፤ በከተማ ደረጃ ያሉ ተመሳሳይ የፍትሕ ተቋማት ደግሞ በጅማ ከተማ አስተዳደር ሥር ለሚገኙ 19 ቀበሌዎች አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው። በተመሳሳይም ሸቤ ሶምቦ በተሰኘው አዋሳኝ ወረዳ በተደረገው ክትትል የሸቤ ሶምቦ ወረዳ ፍርድ ቤት፣ የዐቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤት እና የፖሊስ ጽሕፈት ቤት በወረዳው አስተዳደር ሥር ለሚገኙ 21 የገጠር ቀበሌዎችና 2 የከተማ አስተዳደሮች አገልግሎት እንደሚሰጡ በክትትሉ መረዳት ተችሏል። በዚህም ምክንያት በጅማ ዞን፣ በጅማ ከተማ እና በሸቤ ሶምቦ አዋሳኝ ወረዳ የሚገኙት የፍትሕ ተቋማት ተቋማቶቹ ከሚገኙበት ከተማ ወይም ቀበሌ ውጪ ላለው ማኅበረሰብ በርቀት የሚገኙ በመሆናቸው የፍትሕ አገልግሎት ለማግኘት ለጊዜ እና ለገንዘብ ወጪ እንዲሁም ለእንግልት የሚዳርጉ መሆኑን እና የቦታ ርቀቱ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የተጎጂዎች ፍትሕ የማግኘት መብት ላይ ጫና እየፈጠረ እንደሚገኝ ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው ፖሊሶች እና ዐቃቤያነ ሕግ መረዳት ተችሏል። በጅማ ዞን አንድ ብቻ የተቀናጀ የአንድ ማእከል አገልግሎት ያለ ሲሆን ይህ ማእከልም በጅማ ስር ለሚገኙ 21 ወረዳዎች፣ በአዲሱ ደቡብ ምዕራብ ክልል ስር ለሚገኙ ቦንጋ እና ሚዛን ቴፒ ከተሞች እንዲሁም ከኦሮሚያ ክልል ቦኖ በደሌና መቱ ዞኖች

ለሚመጡ የጥቃት ተጎጂዎች ብቸኛ አገልግሎት ሰጪ ማእከል በመሆኑ የመጓጓዣ ወጪው የገንዘብ ዐቅማቸው አነስተኛ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች ፍትሕ የማግኘት መብታቸውን እንዳይጠቀሙ እክል ሆኗል፡፡

በሐረሪ ክልል ዘጠኝ ወረዳዎች ያሉ ሲሆን ሦስቱ የገጠር ወረዳዎች ስድስቱ ደግሞ የከተማ ወረዳዎች ናቸው፡፡ ስድስቱ የከተማ ወረዳዎች በሥራቸው 19 ቀበሌዎች እንዲሁም በሦስቱ የገጠር ወረዳዎች ደግሞ በሥራቸው 17 ቀበሌዎች አሉ፡፡ በሐረሪ ከተማ የሚገኙት የሐረሪ ክልላዊ መንግሥት ፖሊስ ኮሚሽን፣ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ እንዲሁም የመጀመሪያ ደረጃ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ከቀላል ድብደባ ውጭ ያሉ በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ የጥቃት ወንጀሎችን ፍትሕ በመስጠት ሂደት ውስጥ ኃላፊነት እና ሥልጣን አላቸው፡፡ በመሆኑም በገጠር ወረዳዎች የሚኖሩ የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት ፍትሕን ፍለጋ ካሉበት የገጠር ወረዳ በራሳቸው የገንዘብ ወጪ ወደ ሐረር ከተማ መጓዝ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም በሐረር ከተማ የሚገኙት የፍትሕ ተቋማት ለገጠሩ ወረዳዎች ነዋሪዎች ተደራሽ እንዳይሆኑ አድርጓል፡፡ ተጎጂዎች የጥቃት ወንጀሎችን እንዲያዩ ሥልጣን ለተሰጣቸው በሐረር ከተማ ለሚገኙት የፍትሕ ተቋማት ብቻ ሳይሆን ለገጠር ወረዳ ፍትሕ ቢሮ ወንጀሉን ለማመልከት በእግር ጉዞ ረዥም ጊዜ የሚወስድ እና የመጓጓዣ አገልግሎት ማግኘት አስቸጋሪ መሆኑን በክትትሉ መረዳት ተችሏል፡፡

በክልሉ አንድ የተቀናጀ ማእከል ብቻ ያለ ሲሆን የሚገኘውም በሐረር ከተማ በመሆኑ ከገጠር ወረዳዎች ለሚመጡ የጥቃት ተጎጂዎች የመጓጓዣ ወጪ የሚጠይቅ ነው፡፡ ስለሆነም በሐረሪ ክልል በገጠር ወረዳዎች ለሚገኙ የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት የፍትሕ እና የአንድ ማእከል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ርቀት ያላቸው በመሆኑ የመጓጓዣ ወጪው ለተጎጂዎች ፍትሕ የማግኘት መብት እክል መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

የፍትሕ አሠራር እና አገልግሎት አሰጣጥ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆኑ አስፈላጊውን መገልገያዎች እና አገልግሎቶች እንዲያቀርቡ የዓለም አቀፉ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት ያስገድዳል፡፡[38] የፍትሕ እና የድጋፍ ሰጪ ተቋማት የሕንጻ አሠራር እና አገልግሎት አሰጣጥ አካል ጉዳተኛ እና ጉዳት አልባ የጥቃት ተጎጂዎችን እኩል አገልግሎት መስጠት የሚያስችል መሆን አለበት፡፡ በመሆኑም የፍትሕ ተቋማት መግቢያ በሮች፣ በፍትሕ ተቋማት አገልግሎት የሚሰጡ ቢሮዎች፣ የችሎት አዳራሾች፣ መጸዳጃ ቤቶች እና መተላለፊያ መንገዶች የአካል ጉዳተኛ ተጠቃሚዎችን ፍላጎቶች ያማከሉ ሊሆኑ ይገባል፡፡

ከዚህ አንጻር በአዲስ አበባ ከተማ በተደረገው ክትትል አብዛኛው የአቤቱታ መቀበያ እና ምርመራ የሚደረግባቸው የፖሊስ መምሪያ ቢሮዎች እና ዐቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤቶች በአማራጭ የቀረበ አሳንሰር ያልተገጠመላቸው፣ መግቢያዎቹ የተሽከርካሪ ወንበር መወጣጫ ተዳፋት (ራምፕ) የሌላቸው ወይም ተሽከርካሪ ወንበር ማሳለፍ የማያስችሉ፣ ተሽከርካሪ ወንበር የሚጠቀሙ ባለጉዳዮችም ከአንድ ክፍል ወደሌላ ሌላ ክፍል በቀላሉ ለመዘዋወር የሚያስችል ሰፋፊ በሮች የሌሏቸው እንዲሁም መጸዳጃ ቤቶቹም በተመሳሳይ ተሽከርካሪ ወንበሮችን ማስገባት የማይችሉ

[38] Convention on the rights of persons with disabilities (hereinafter referred to as ‘CRPD’) Principle 2

መሆኑን በክትትሉ መረዳት ተችሏል፡፡ ክትትል በተካሄደባቸው ፍርድ ቤቶች መግቢያ በሮች ላይ ተዳፋት የገነቡ እና አሳንሰር የተገጠመላቸው ቢሆንም የተወሰኑት አሳንሰሮች በብልሽት ምክንያት የቆሙ፣ አሳንሰሮች በሚሰሩባቸው የፍርድ ቤት ተቋማት ደግሞ ለዐይነ ስውራን በሚመች መልኩ የደረሱበትን ወለል ማወቅ የማያስችሉ ናቸው፡፡

በተመሳሳይ በኦሮሚያ ክልል በሸገር ከተማ አስተዳደር በቡራዩ እና በሰበታ ክፍለ ከተሞች እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን፣ በጅማ ከተማ እና በሸቤ ሶምቦ አዋሳኝ ወረዳ እንዲሁም በሐረሪ ክልል በሐረር ከተማ እና በኤረር አዋሳኝ ወረዳ የሚገኙ የፍትሕ ተቋማት ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ያልሆኑ በተለይም ተሽከርካሪ ወንበሮችን ማስገባት የማይችሉ መሆኑን በክትትሉ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በጅማ ከተማ የሚገኘው የተቀናጀ የአንድ ማእከል አገልግሎት ተቋም መግቢያ ራምፕ የተሰራለት ቢሆንም መተላለፊያዎች እና መጸዳጃ ቤቶቹ ተሽከርካሪ ወንበር ለሚጠቀሙ ተጎጂዎች ምቹ ያልሆኑ ወይም ተሽከርካሪ ወንበሮችን ማስገባት የማይችሉ መሆኑን በክትትሉ መረዳት ተችሏል፡፡

በሐረር ከተማ የሚገኘው የተቀናጀ የአንድ ማእከል በጀጎል ጠቅላላ ሆስፒታል ውስጥ ይገኛል፡፡ ማእከሉ በሆስፒታሉ አንደኛው ፎቅ ላይ የሚገኝ ሲሆን መወጣጫው ጠባብ እና አካል ጉዳተኛን ታሳቢ ያላደረገ በመሆኑ አካል ጉዳተኛ ተጎጂዎች ወደ ማእከሉ ሲመጡ ተሸክመው እንደሚያስገቧቸው ቃለመጠይቅ ከተደረገላቸው የማእከሉ ባለሙያዎች እና ከተደረገው ምልከታ መረዳት ተችሏል፡፡ ይህ ሆስፒታል ከተመሠረተ ከ125 ዓመት በላይ ያስቆጠረና በዩኔስኮ በታሪክ ቅርስነት የተመዘገበ  ቢሆንም ሕንጻው የአካል ጉዳተኞችን ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ ማሻሻያዎች ሊደረግለት አልተቻለም፡፡

ሌላው የተደራሽነት መገለጫ የፍትሕ እና የድጋፍ ሰጪ ተቋማት ለሥራ ከሚጠቀሙባቸው የሥራ ቋንቋዎች ውጪ ለሚናገሩ ሰዎች ተደራሽ መሆን ነው፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ በተከናወነው ክትትል የአቤቱታ ቅበላ እና ምርመራ የሚከውኑ የፖሊስ መምሪያ እና የዐቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤቶች ከአማርኛ ቋንቋ ውጪ ለሚናገሩ ሰዎች ተደራሽ አይደሉም፡፡ የፖሊስ መምሪያ እና የዐቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋን መረዳት ለማይችሉ የወሲባዊ ጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት የትርጉም ባለሙያ ወይም አስተርጓሚ የላቸውም፡፡ የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት ወደ ተቋማቱ በሚመጡበት ጊዜ ፈቃደኛ የሆነ የተጎጂውን ቋንቋ መናገር እና መስማት የሚችል ግለሰብ በመፈለግ እንደሚስተናገዱ እና አስተርጓሚ ካልተገኘ የፍትሕ ተቋሙን አገልግሎት ማግኘት እንደሚቸገሩ በክትትሉ ታውቋል፡፡ ክትትሉ በተካሄደባቸው የፖሊስ መምሪያዎች፣ የዐቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤቶች እና ፍርድ ቤቶች መስማት ለተሳናቸው የጥቃት ተጎጂዎች የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ እንደሌለ እና የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ የሚሹ የጥቃት ተጎጂዎች ወደ ፍትሕ ተቋማት በሚመጡበት ጊዜ መስማት ከተሳናቸው ማኅበር ትብብር በመጠየቅ እንደሚያስተናግዷቸው መረዳት ተችሏል፡፡

በኦሮሚያ ክልል በሸገር ከተማ አስተዳደር በቡራዩ እና በሰበታ ክፍለ ከተሞች፣ በጅማ ዞን፣ በጅማ ከተማ እና በሸቤ ሶምቦ አዋሳኝ ወረዳ፣ እንዲሁም በሐረሪ ክልል በሐረር ከተማ እና በኤረር አዋሳኝ ወረዳ በተደረገው ክትትል በእነዚህ አካባቢዎች የሚገኙ የፍትሕ እና የተቀናጀ የአንድ

ማእከል ተቋማት የሥራ ቋንቋቸውንመረዳት ለማይችሉ የጥቃት ተጎጂዎች የምልክት ቋንቋን ጨምሮ የትርጉም አገልግሎት የሌላቸው መሆኑን መረዳት ተችሏል:: በዚህም ምክንያት በተጠቀሱት አካባቢዎች ያሉ የፍትሕ ተቋማት የሥራ ቋንቋቸውንመረዳት ለማይችሉ እንዲሁም መስማት ለተሳናቸው የጥቃት ተጎጂዎች ተደራሽ አይደሉም::

የመረጃ ተደራሽነት ሌላኛው የፍትሕ ተደራሽነት ማሳያ ነው:: በአዲስ አበባ ከተማ፣ በኦሮሚያ ክልል በሸገር ከተማ አስተዳደር በቡራዩ እና በሰበታ ክፍለ ከተሞች፣ በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን፣ በጅማ ከተማ እና በሸቤ ሶምቦ አዋሳኝ ወረዳ እንዲሁም በሐረሪ ክልል በሐረር ከተማ እና በኤረር አዋሳኝ ወረዳ በተደረገው ክትትል ተጎጂዎች ስለደረሰባቸው ጥቃት የት ማመልከት እንዳለባቸው በአቅራቢያቸው ወደሚገኙ ፖሊስ ጣቢያዎች በመሄድ መረጃ ከማግኘት ባለፈ በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ በሚያልፉበት ጊዜ ወጥ የሆነ አስፈላጊ መረጃዎችን የሚያገኙበት የመረጃ ማእከላት በፍትሕ ሥርዓቱት እንደሌለ የክትትሉ ግኝት ያሳያል::

### 3.2 ክብርን በጠበቀ እና ለዳግም ጥቃት በማያጋልጥ መልኩ የመስተናገድ መብት

ክትትሉ በሸፈናቸው ሁሉም አካባቢዎች ተሳታፊ የሆኑ የፍትሕ እና የድጋፍ ሰጪ አካላት የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ሲያልፉ ክብራቸውን በጠበቀ መልኩ እንደሚስተናገዱ ቢገልጹም የጥቃት ተጎጂ ሴቶችን እና ሕፃናትን እንዲያስተናግዱ የተመደቡት የፍትሕ አካላት ከመደበኛው የፖሊስ፣ የዐቃቤ ሕግ እና የዳኞች ስልጠና ውጪ በተለየ ሁኔታ የጥቃት ተጎጂዎችን ሥነ ልቦና ያማከለ የመብት አያያዝን እንዲረዱ የሚያስችሉ አስፈላጊ ስልጠናዎችን እንዳልወሰዱ መረዳት ተችሏል:: በዋናነትም ፍረጃን እና አግባብ ያልሆኑ አመለካከቶችን፣ በሴቶች እና ሕፃናት ላይ ስለሚፈጸሙ ጥቃቶች እና ምላሽ አሰጣጥ፣ እንዲሁም ሰብአዊ መብቶችን የተመለከቱ ልዩ ስልጠናዎችን ያልወሰዱ መሆናቸውን፣ በፍትሕ አስተዳደር ስትራቴጂ ወይም ዕቅድ ውስጥም ለፍትሕ አካላት በመደበኛነት ስልጠና እንዲሰጥ እንደማይደረግ መረዳት ተችሏል:: ሆኖም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አልፎ አልፎ በሴቶችና በሕፃናት ጥቃቶች ዙሪያ የሚሰጡ ስልጠናዎች እንዳሉ ቃለመጠይቅ ከተደረገላቸው የፖሊስ አባላት፣ ዐቃቤያነ ሕግ እና ዳኞች አስረድተዋል::

የጥቃት ተጎጂዋ ለአካላመጠን የደረሰች ሴት በምትሆንበት ጊዜ ጥቃት ስለመፈጸሙ ለማረጋገጥ በሚደረግ ጥረት ተጎጂዋ የምትሰጠውን መረጃ እንዲሁም ምስክርነት መጠራጠር፣ ተጎጂዎችን ጥፋተኛ ማድረግ፣ ጥቃቱን የማቅለል እና መሰል ሰብአዊ ክብርን የሚነኩ ድርጊቶች በአንዳንድ የፍትሕ አካላት ሊፈጸሙ እንደሚችሉ ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው የፍትሕ አካላት እንዲሁም በፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ካለፉ የጥቃት ተጎጂዎች መረዳት ተችሏል:: ከላይ እንደተገለጸው የጥቃት ተጎጂዎች በተመሳሳይ ወይም በተለያየ የፍትሕ አካላት በተደጋጋሚ ቃለ መጠይቅ መደረግ ለሁለተኛ ደረጃ ጥቃት ወይም ጉዳት አጋላጭ ምክንያት ነው::

በአዲስ አበባ ከተማ በተደረገው ክትትል የወሲባዊ ጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት ስለተፈጸመባቸው ጥቃት በተደጋጋሚ ለተለያዩ የፍትሕ እና የድጋፍ ሰጪ አካላት እንዲያስረዱ እንደሚደረጉ እና በዚህም ምክንያት ከሚደርስባቸው ሁለተኛ ደረጃ ጥቃት ወይም ጉዳት ለማገገም የሚረዱ

የሥነልቦና አገልግሎቶች አለመኖሩ የክትትሉ ውጤት ያሳያል። የወሲባዊ ጥቃት ተጎጂዎች ጥቃቱ ከተፈጸመ በኋላ በአካባቢያቸው ለሚገኘው ፖሊስ መምሪያ ስለ ደረሰው ጥቃት ያስረዳሉ፤ ከዚያም ሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ወሲባዊ ጥቃቶችን የሚመለከተው የክፍለ ከተማው ፖሊስ መምሪያ በመሆኑ ወደዚያው እንዲያመሩ ይደረጋሉ። በመቀጠል ለክፍለ ከተማው ፖሊስ መምሪያ ስለጥቃቱ ካስረዱ በኋላ በአቅራቢያ ወደሚገኘው የተቀናጀ የአንድ ማእከል አገልግሎት ለሕክምና ምርመራ እንዲሄዱ ይደረጋሉ። ፖሊስ የሕክምናውን ማስረጃ ጨምሮ ያደራጀውን ማስረጃ ለዐቃቤ ሕግ ይልካል። ዐቃቤ ሕግም የደረሰውን የፖሊስ ማስረጃ ለመመርመር የጥቃት ተጎጂዋን በድጋሚ በመጥራት ጉዳዩን እንድታስረዳ ያደርጋል። ፍርድ ቤትም እንደአስፈላጊነቱ በተደጋጋሚ ጉዳዩን እንድታስረዳ ሊያደርግ ይችላል።

በኦሮሚያ ክልል በሸገር ከተማ አስተዳደር በቡራዩ እና በሰበታ ክፍለ ከተሞች፣ በጅማ ዞን፣ በጅማ ከተማ እና በሸቤ ሶምቦ አዋሳኝ ወረዳ እንዲሁም በሐረሪ ክልል በሐረር ከተማ እና በኤረር አዋሳኝ ወረዳ በተደረገው ክትትልም እንዲሁ ተጎጂዎች ጉዳያቸውን በተደጋጋሚ በማስረዳት ምክንያት የሚደርስባቸውን ሁለተኛ ደረጃ ጉዳት ለማስወገድ የተዘረጋ ሥርዓትም ሆነ አሠራር አለመኖሩንና ሁሉም የፍትሕ ተቋማት ለጉዳዩ አስፈላጊ ነው ብለው ባመኑ ጊዜ ሁሉ ተጎጂዎች ጉዳያቸውን በተደጋጋሚ እንዲያስረዱ እንደሚያደርጉ ከክትትሉ መረዳት ተችሏል። ከላይ እንደተገለጸው የጥቃት ተጎጂዎች በተደጋጋሚ ከጥቃት አድራሹ ተጠርጣሪ ጋር በፍትሕ ሂደት መገናኘት ለሁለተኛ ደረጃ ጉዳት አጋላጭ ምክንያት ነው። (ይህ ጉዳይ በዚህ ሪፖርት ክፍል 3.3. ተመልክቷል።)

### 3.3 ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ የፍትሕ አገልግሎት የማግኘት መብት

በአዲስ አበባ ከተማ በተደረገው ክትትል የወሲባዊ ጥቃት የአቤቱታ መቀበያ እና ምርመራ የሚደረጉባቸው ክፍሎች ምስጢራዊነተቱን ያልጠበቀ፣ ሦስተኛ ወገኖች ስለ ተጎጂ ማንነት እና ስለጥቃቱ ዐይነት በቀላሉ ለመረዳት እና ለማወቅ የሚችሉበት መሆኑን ለመረዳት ተችሏል። በተጨማሪም በወንጀል ምርመራ ክፍሎች የጥቃት ተጎጂዎች ቃል ሲሰጡ ከመርማሪ ፖሊስ ውጪ ሌሎች የፖሊስ አባላት በተገኙበት ስለጥቃቱ እንዲያስረዱ የሚደረጉበት ሁኔታዎች እንዳሉም መረዳት ተችሏል።

በችሎት ጊዜም እንዲሁ ተጎጂዋ ለአካለ መጠን የደረሰች በምትሆንበት ጊዜ ዳኞች በራሳቸው ተነሳሽነት ወይም በዐቃቤ ሕግ ወይም በተከሳሽ ክርክሩ በዝግ ችሎት እንዲሆን ለፍርድ ቤት ካልተጠየቀ በስተቀር ክርክሩ የሚካሄደው በግልጽ ችሎት እንደሆነ መረዳት ተችሏል። በመሆኑም ተጎጂዋ በፍርድ ቤት የምስክርነት ቃሏን የምትሰጠው ጥቃት በማድረስ የተጠረጠረው ሰው ባለበት እና ችሎቱን ለመከታተል በተገኙ ሰዎች ፊት ነው። ጉዳዩ በግልጽ ችሎት መካሄዱ እና ተጠርጣሪው እና ተጎጂዋ ፊት ለፊት እንዲገናኙ መሆኑ ተጎጂዋን ለሥነ ልቦናዊ ጫና እና ለሁለተኛ ደረጃ ጉዳት የሚያጋልጥ ነው። ነገር ግን የጥቃት ተጎጂዎቹ ሕፃናት በሚሆኑበት ጊዜ ችሎቱ በዝግ እንደሚካሄድ እና ምስክርነት የሚሰጡትም በደኅንነት ካሜራ (CCTV Camera) ታግዘው በመሆኑ ተጠርጣሪውን የሚያዩበትም ሆነ ድምፁን የሚሰሙበት አጋጣሚ አነስተኛ ነው። ይህም የሕፃናት የችሎት ሥርዓት አካለ መጠን የደረሱ ሴቶች ከሚያገኙት የችሎት

አገልግሎት በተሻለ ሁኔታ ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ ለማድረግ አበረታች ጅማሬዎች እንዳሉ ያሳያል።

በኦሮሚያ ክልል በሸገር ከተማ አስተዳደር በቡራዩ እና በሰበታ ክፍለ ከተሞች በተደረገው ክትትል በሰበታ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት የሚስተናገዱበት የተለየ ክፍል ቢኖርም በሁለቱም ክፍለ ከተሞች በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን አስመልክቶ በዐቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤትም ሆነ በፍርድ ቤት የተለየ መዋቅር የሌለና የጥቃት ጉዳዮች እና ተጎጂዎች የሚታዩበት እና የሚስተናገዱት ሁኔታ ከሌሎች የወንጀል ዐይነቶች የተለየ አለመሆኑን በቃለመጠይቅ እና በምልከታ ለማወቅ ተችሏል። በመሆኑም የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት ለምርመራ ሥራም ሆነ በችሎት ጉዳያቸውን እንዲያስረዱ የሚደረጉት ሌሎች ባለጉዳዮች እና ሠራተኞች ባሉበት ወይም ሦስተኛ ወገን ስለጥቃቱ መስማት በሚችልበት ሁኔታ ነው። በተመሳሳይ በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን፣ በጅማ ከተማ እና በሸቤ ሶምቦ አዋሳኝ ወረዳ እንዲሁም በሐረሪ ክልል በሐረር ከተማ እና በኤረር አዋሳኝ ወረዳ የሚገኙ የፍትሕ ተቋማት በሴቶችና ሕፃናት የሚፈጸሙ ጥቃቶችን አስመልክቶ የተለየ መዋቅር የሌላቸው በመሆኑ የጥቃት ጉዳዮች እና ተጎጂዎች የሚታዩበት እና የሚስተናገዱት ሁኔታ ከሌሎች የወንጀል ዐይነቶች የተለየ አለመሆኑን መረዳት ተችሏል። ሆኖም በሐረሪ ክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሕፃናት ችሎት የተቋቋመ በመሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ውጪ የተጎጂዋ/ው ሕፃን ማንነት ሳይታወቅ ችሎት እንደሚካሄድ በቃለ መጠይቅ እና በምልከታ መረዳት ተችሏል።

### 3.4 የደኅንነት ጥበቃ የማግኘት መብት

በአዲስ አበባ ከተማ በተደረገው ክትትል አቤቱታ የሚቀበለው ወይም ምርመራ የሚያካሂደው ፖሊስ በተጎጂ ላይ የደኅንነት ሥጋት እንዳለ ከተረዳ ወይም ተጎጂዋ የደኅንነት ሥጋት እንዳለባት ከገለጸች መንግሥታዊ ካልሆኑ የመጠለያ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ትብብር በመጠየቅ በመጠለያ ጣቢያ ለመቆየት እንዲችሉ ወደ ተቋማቱ እንደሚላኩ ለመረዳት ተችሏል። ይህ የቅብብሎሽ ሥርዓት በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን እና መንግሥታዊ ባልሆኑ የመጠለያ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በተደረገ ስምምነት ተግባራዊ የሚደረግ ነው። ሆኖም እነዚህ በከተማው የሚገኙት መንግሥታዊ ያልሆኑ የመጠለያ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጥቂት እና የዐቅም ውስንነት ያለባቸው በመሆኑ በደኅንነት ሥጋት ምክንያት መጠለያ ለሚሹ የጥቃት ተጎጂዎች ሁሉ ተደራሽ አይደሉም።

በኦሮሚያ ክልል በሸገር ከተማ አስተዳደር በሰበታ ክፍለ ከተማ 'ሲቄ' የተሰኘ እና በጅማ ከተማ "ሰው ለሰው" የተሰኘ መንግሥታዊ ያልሆኑ የመጠለያ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ያሉ ቢሆንም፤ በዐቅም ውስንነት ምክንያት ተደራሽ አይደሉም። በኦሮሚያ ክልል በሸገር ከተማ አስተዳደር በቡራዩ ክፍለ ከተማ እና በሐረሪ ክልል የመጠለያ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት የሉም። በመሆኑም የደኅንነት ስጋት ያለባቸውን የጥቃት ተጎጂዎች በጊዜያዊነት ለመጠበቅ በፖሊሶች መኖሪያ ቤት፣ ተባባሪ በሆነ ግለሰብ መኖሪያ ቤት ወይም ዘመድ ቤት፣ ማረሚያ ቤት፣ ፖሊስ ጣቢያ እና ሆስፒታል እንዲቆዩ እንደሚደረግ ሆኖም የምግብና ሌሎች አስፈላጊ አቅርቦቶች በመንግሥት በጀት የማይያዝላቸው መሆኑን የፍትሕ እና የድጋፍ ሰጪ አካላት ለኮሚሽኑ

አስረድተዋል። ከእነዚህ ጊዜያዊ ስፍራዎች ውስጥም ሴቶችና ሕጻናትን ለዳግም ጥቃት አጋላጭ የሆኑ ናቸው። በአጠቃላይ ክትትሉ በተከናወነባቸው ሁሉም አካባቢዎች የጥቃት ተጎጂዎች አቤቱታ ከማቅረብ ጀምሮ በፍትሕ ሥርዓቱ በሚያልፉበት ጊዜ ከጥቃት አድራሹ ተጠርጣሪ፣ ከማኅበረሰቡ ወይም ከማንኛውም ሦስተኛ ወገን ከሚመጣ የሁለተኛ ደረጃ ጉዳት እና ዳግም ጥቃት የሚጠብቅ ወጥ የሆነ አሠራር በፍትሕ አስተዳደሩ አለመኖሩን ያሳያል።

### 3.5 የመሰማት/ የመሳተፍ መብት

በአዲስ አበባ ከተማ፣ በኦሮሚያ ክልል በሸገር ከተማ አስተዳደር በቡራዩ እና በሰበታ ክፍለ ከተሞች፣ በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን፣ በጅማ ከተማ እና በሸቤ ሶምቦ አዋሳኝ ወረዳ እንዲሁም በሐረሪ ክልል በሐረር ከተማ እና በኤረር አዋሳኝ ወረዳ በተደረገው ክትትል የጥቃት ተጎጂዎቹ ስለ ጥቃቱ መፈጸም ዋነኛ የመረጃ ምንጭ እንደመሆናቸው አቤቱታ በሚቀርብበት እና በምርመራ ወቅት እንዲሁም በችሎት ክርክር ጊዜ ስለ ጥቃቱ እንዲያስረዱ ሰፊ ዕድል እንደሚሰጣቸው መረዳት ተችሏል። ሆኖም ስለጥቃቱ የክስ ጉዳይ፣ የምርመራ ሂደት፣ ስለተጠርጣሪው በቁጥጥር ሥር መዋል/አለመዋል፣ በጊዜ ቀጠሮ ስለሚኖር የዋስትና ውሳኔ፣ ስለተጎጂዋ የደኅንነት ሥጋት እንዲሁም በክስ መዝገቡ በሚወሰኑ ውሳኔዎች የጥቃት ተጎጂዎችን አሳታፊ የሚያደርግ ወጥ የሆነ አሠራር የለም።

የሕፃናትን የመሰማት መብት ለማረጋገጥ ከሚወሰዱ እርምጃዎች አንጻር ክትትሉ በተካሄደባቸው ሁሉም አካባቢዎች የጥቃት ተጎጂ ሕፃናት የአቤቱታ መቀበያ እና የምርመራ ክፍሎች እንዲሁም ቅጥር ግቢዎቹ ለሕፃናት ምቹት የማይሰጡ፣ በርካታ መለዮ የለበሱ የፖሊስ አባላት የሚገኙበት፣ ስለጥቃቱ በንግግር መግለጽ ለማይችሉ ወይም ለማይፈልጉ ሕፃናት አስፈላጊ የሆኑ መገልገያዎች የሌሉበት እንዲሁም ሕፃናትን ከስሜት መረበሽ እንዲወጡ የሚያግዙ መገልገያዎች ያልተሟሉበት እንዲሁም በፖሊስ መምሪያም ሆነ በዐቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤት የሥነልቦና ወይም የማኅበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች በበቂ ሁኔታ ባለመመደባቸው ምክንያት ያለባለሙያ እገዛ እንደሚስተናገዱ በክትትሉ መረዳት ተችሏል።

በአንጻሩ በአዲስ አበባ እና በሐረሪ ክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች የጥቃት ተጎጂ ሕፃናት በችሎት ምስክርነት የሚሰጡት በሥነ ልቦና ወይም በማኅራዊ ሳይንስ ባለሙያ ታግዘው እንደሆነና ፍርድ ቤቶቹም ለዚሁ ዓላማ ባለሙያዎችን እንደሚመደቡ መረዳት ተችሏል። በተጨማሪም ምስክርነት የሚሰጡባቸው ክፍሎች የፍርሀት ስሜት እንዳይፈጥሩ የልጆች መጫወቻ እና ስዕል መሳያ ቁሳቁስ ለማሟላት ጥረት ይደረጋል ። ሆኖም ክትትሉ በተካሄደባቸው ሁሉም አካባቢዎች ሕፃናትን ከአቤቱታ ቅበላ እስከ ውሳኔ የሚያስተናግዱ የፍትሕ ባለሙያዎች በሕፃናት መብትና ፍላጎት ላይ ያልሰለጠኑ ናቸው።

### 3.6 የተፋጠነ ፍትሕ እና ውጤታማ መፍትሔ የማግኘት መብት

በአዲስ አበባ ከተማ በተደረገው ክትትል ወሲባዊ ጥቃትን አስመልክቶ በፖሊስ መምሪያ፣ በዐቃቤ ሕግ እና በፍርድ ቤት የተለየ የሥራ ክፍል መኖሩ ጉዳዮችን በፍጥነት ውሳኔ እንዲያገኙ

እንደሚረዳ መገንዘብ ተችሏል፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 በአንቀጽ 19 (ሰ) "የየፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንቶች ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት የተፈጸመባቸው ሴቶች፣ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያንን አስመልክቶ በፍርድ ቤቶች የሚከፈቱ መዝገቦች በተፋጠነ ፍትሕ አገልግሎት እልባት እንዲያገኙ እና የሕግ ባለሙያ ድጋፍ እንዲሰጣቸው ያደርጋሉ" ሲል ይደነግጋል፡፡ ይህ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በሴቶች እና በሕፃናት የሚፈጸሙ ጥቃቶችን እልባት ለመስጠት የተፋጠነ ፍትሕ የመስጠት አሠራር እንዲኖራቸው ይረዳል፡፡ ሆኖም ጉዳዮች በፍጥነት እልባት እንዳያገኙ የሕክምና ማስረጃ በሚፈለገው ጊዜ እና ይዘት አለመቅረብ እንዲሁም የተከሳሽ እና የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች አለመገኘት ጉዳዮችን እንደሚያዘገይ ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው የፍትሕ አካላት አስረድተዋል፡፡

በኦሮሚያ ክልል በሸገር ከተማ አስተዳደር በቡራዩ እና በሰበታ ክፍለ ከተሞች፣ በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን፣ በጅማ ከተማ እና በሸቤ ሶምቦ አዋሳኝ ወረዳ እንዲሁም በሐረሪ ክልል የሴቶችና ሕፃናትን ጥቃት ብቻ የሚመለከት መዋቅር አለመኖር፣ የሕክምና ማስረጃ በሚፈለገው ጊዜ እና ይዘት አለመቅረብ እንዲሁም የተከሳሽ እና ምስክሮች አለመገኘት ጉዳዮች በፍጥነት ውሳኔ እንዳያገኙ ምክንያት እንደሆኑ በክትትሉ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ዳኞች ገልጸዋል፡፡

የጥቃት ተጎጂ ሴቶች እና ሕፃናት ውጤታማ መፍትሔ እንዲያገኙ ጥቃት ስለመፈጸሙ እንዲያሳይ የሚፈለገው ማስረጃ እጅግ ጥብቅ እንዳይሆን ሀገራት የማስረጃ ሕጎቻቸውን እንዲገመግሙ የሲዳው ኮሚቴ ምክረ ሐሳብ ቁጥር 33 አንቀጽ 51(ሸ) ያሳስባል፡፡ በተጨማሪም ውጤታማ መፍትሔ ለተጎጂዎች የሚሰጡ ካሳን ጨምሮ ያሉ የፍትሐ ብሔር መፍትሔዎችን ሊያካትት እንደሚገባ ይመክራል፡፡

ከዚህ አንጻር በክትትሉ በሴቶች እና በሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ከሌሎች የወንጀል ዐይነቶች በተለየ በባህሪያቸው ድብቅ በመሆናቸው ጥቃት ስለመፈጸሙ ዋነኛ የማስረጃ ምንጭ የጥቃት ተጎጂው የምስክርነት ቃል ላይ እንዲወሰን ያደርገዋል፡፡ ክትትል የተደረገባቸው ሁሉም የፍትሕ አካላት የወሲባዊ ጥቃት የምርመራ ሥርዓቱ አለመዘመን ሳቢያ የወንጀል ምርመራው በዋናነት ተጎጂዋ በምትሰጣቸው ማስረጃዎች ላይ መሠረት ያደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም የማስረጃ ምዘናው እንደ ሌሎች የወንጀል ዐይነቶች 'ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ' ማስረዳት አዳጋች በመሆኑ የስሚ ስሚን ጨምሮ ወንጀሉ ስለመፈጸሙ በቀጥታ ሊያሳዩ የማይችሉ ማስረጃዎችን እንደሚቀበሉ ከፍትሕ አካላት ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ መረዳት ተችሏል፡፡ ሆኖም በሴቶች እና ሕፃናት ችሎቶች 'በቂ እና አሳማኝ' በሆነ ማስረጃ ተጠርጣሪውን ተጠያቂ ያደረገ ውሳኔ ወደ ይግባኝ በሚሄድበት ጊዜ ይግባኝ የተጠየቀበት የበላይ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በመደበኛ የወንጀል ችሎት ስለሚያይ መደበኛ የሆነ የማስረጃ ምዘና ደንቦችን መሠረት በማድረግ የታችኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ ውድቅ ሊያደርግ እንደሚችል መረዳት ተችሏል፡፡

የጥቃት አድራሹን ተጠያቂነት ተከትሎ ተጎጂዎች በደረሰባቸው ጉዳት ልክ ፈጣን የሆነ የካሳ እና የማገገሚያ አገልግሎት የማግኘት መብት እንዳላቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መርሖች እና ድንጋጌዎች ቢገልጹም ክትትሉ በተካሄደባቸው ሁሉም የፍትሕ ተቋማት ጥቃት አድራሹን የወንጀል ተጠያቂ ከማድረግ ባለፈ ፍርድ ቤቱ የገንዘብ ካሳን ጨምሮ ተጎጂዎች ከደረሰባቸው ጉዳት እንዲያገግሙ የሚረዱ የጤና፣ የሥነ ልቦና እና የማኅበራዊ አገልግሎቶችን አስመልክተው ትዕዛዝ እንደማይሰጡ መረዳት ተችሏል። የወንጀል ሕጉ የካሳ ክፍያን በወንጀል ችሎት አጣምሮ መጠየቅ እንደሚቻል በአንቀጽ 101 የገለጸ ቢሆንም፤ የወንጀል እና የካሳ ጥያቄ አጣምሮ መጠየቅ ያልተለመደ እንደሆነ መረዳት ተችሏል።

## 3.7 የድጋፍ አገልግሎት የማግኘት መብት

የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫዎች ለወሲባዊ ጥቃት ተጎጂዎች አፋጣኝና የተሟላ የሕክምና አገልግሎትና የፎረንሲክ ማስረጃ ማሰባሰብ፣ የምክርና የድጋፍ አገልግሎት እንዲሁም የፖሊስ፣ ዐቃቤ ሕግና የመሳሰሉትን የሕግ አገልግሎት ሊሰጡ እንደሚገባ በ2001 ዓ.ም. የወጣው በፍትሕና እንክብካቤ ማዕከል ውስጥ ለሚሳተፉ አገልግሎት ሰጪዎች የተዘጋጀው የሥራ ማስፈጸሚያ መመሪያ ያሳስባል። እነዚህ ማእከላት አስፈላጊ ሲሆን ለሚመለከተው አገልግሎት ሰጪ የሚመሩበት ሥርዓት (referral system) ሊኖራቸው እንደሚገባ ያስቀምጣል።

ሆኖም በዚህ ሪፖርት የኢኮኖሚያዊ ተደራሽነት በሚለው ክፍል እንደተመለከተው የተቀናጀ የአንድ ማእከል አገልግሎት የሕግ፣ የሕክምና፣ የሥነ ልቦና ድጋፍ እና ሌሎች የድጋፍ አገልግሎቶች ለመስጠት የተቋቋሙ ቢሆንም፤ ለተወሰነ ጊዜ የፖሊስ እና የዐቃቤ ሕግ የሥራ ክፍሎች በማእከላቱ ከመሥራታቸው በስተቀር፤ ክትትል በተደረገበት ወቅት መርማሪ ፖሊስ እና ዐቃቤያን ሕጎች በማእከሉ እንደማይገኙ ለማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም ክትትል በተደረገባቸው ሁሉም አካባቢዎች የማእከላቱ ብዛት እጅግ አነስተኛ በመሆኑ ለማኅበረሰቡ ያላቸው ተደራሽነት እጅግ ውስን መሆኑን መረዳት ተችሏል።

## 3.8 በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ የጥቃት ተጎጂ የሆኑ ሴቶችና ሕፃናት መብት ጥሰት ምክንያቶች

ከላይ ለተገለጹት የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት መብት አያያዝ ሁኔታዎች ምክንያቶቹ በርካታ ሲሆኑ በክትትሉ የተለዩት መሠረታዊ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

1. የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲው የጥቃት ተጎጂ የሆኑ ሴቶችና ሕፃናት ስለሚኖራቸው የመብቶች አያያዝ ከዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ማዕቀፎች ጋር በሚጣጣም መልኩ ዕውቅና ቢሰጥም፣ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕጉ በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን አስመልክቶ ከመደበኛው የወንጀል ሥነ ሥርዓት የተለዩ የሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎችን አላስቀመጠም። ከመደበኛው የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ውጪ በወንጀል ፍትሕ አስተዳደሩ የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናትን የመብቶች አያያዝን የሚደነግግ ወጥና አስገዳጅ የሆነ የሥነ ሥርዓት መመሪያ ወይም ፕሮቶኮል የለም።

2. የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናትን የመብቶች አያያዝን የሚደነግግ ወጥና አስገዳጅ የሆነ የሥነ ሥርዓት መመሪያ ወይም ፕሮቶኮል ባለመኖሩ ለሁሉም የጥቃት ተጎጂ የሆኑ ሴቶችና ሕፃናት ወጥ የሆነ የመብቶች አያያዝ ወይም አሠራር እንዳይኖር ምክንያት ሆኗል። በአዲስ አበባ ከተማ የወሲባዊ ጥቃት ወንጀል ከመደበኛው አሠራር በተለየ በሴቶችና ሕፃናት የፖሊስ፣ የዐቃቤ ሕግ እና የፍርድ ቤት አወቃቀር የሚታይ ሲሆን፤ ሌሎች የጥቃት ዐይነቶች ግን በመደበኛው የወንጀል ፍትሕ ሂደት ይታያሉ። በፍርድ ቤቶች የሴቶችና ሕፃናት ችሎት አደረጃጀት በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ደረጃ ብቻ ያለ በመሆኑ ጉዳዩ በከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚታይበት ጊዜ በመደበኛ የወንጀል ፍትሕ ሂደት የሚያልፉ ይሆናል።
3. የጥቃት ተጎጂ ለሆኑ ሴቶችና ሕፃናት የሚሰጡ እንደ መጠለያ፣ ማገገሚያ፣ ሕክምና፣ የሥነ ልቦና አገልግሎት ያሉ መፍትሔዎች በሀገሪቱ የፍትሐ ብሔር ሕግ ዕውቅና አልተሰጣቸውም። የወንጀል ሕጉ የካሳ ክፍያን በወንጀል ችሎት አጣምሮ መጠየቅ እንሚቻል በአንቀጽ 101 የገለጸ ቢሆንም፤ ገና የተለመደ አሠራር አይደለም።
4. በ2001 ዓ.ም. ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ተጎጂዎች የተቀናጀ ሁሉን ዓቀፍ፣ ሁለገብ ባለሙያን ያቀፈ፣ ጊዜውን የጠበቀ፣ ሥልታዊና ቀጣይነት ያለው ምላሽ መስጠት የሚያስችል ቅንጅታዊ አሠራር ለመዘርጋት መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ የባለድርሻ አካላት፣ በዋናነት የጤና ሚኒስቴር፣ የፍትሕ ሚኒስቴር፣ ፖሊስ፣ የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ ፍርድ ቤቶች፣ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ የመጠለያ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት እንዲሁም መንግሥታዊ ያልሆኑ በወሲባዊ ጥቃት ዙሪያ የሚሠሩ ድርጅቶች በቅንጅትና በትብብር ለመሥራት መግባባት ላይ ተደርሶ ነበር። በማእከላቱ የሚሰጡት አገልግሎቶች ደረጃቸውን የጠበቁ እና የተደራጁ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲሁም ወጥ የሆነ የአሠራር ሥርዓት የተከተሉ እንዲሆኑ ለማስቻል የሚረዳ የአሠራር ሥርዓት ማኑዋልም በ2014 ዓ.ም. ተዘጋጅቶ ነበር። ሆኖም ማእከላቱ በተዘጋጀው የአሠራር ሥርዓት ማኑዋል መሠረት እየሠሩ አለመሆኑን መረዳት ተችሏል።

# ክፍል አራት

## ማጠቃለያ እና ምክረ ሐሳቦች

### 4.1 ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ ስምምነቶች እንዲሁም በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ የጥቃት ተጎጂ ሴቶች እና ሕፃናት ለደረሰባቸው ጥቃት ውጤታማ መፍትሔ ለማግኘት የሚያስችሏቸው የማይነጣጠሉ መብቶች አሏቸው። መንግሥትም ይህንን የማክበር፣ የማስጠበቅ እና የማሟላት ተነፃፃሪ ግዴታውን ለመወጣት የሚያስችሉ ሕግጋትን የማውጣት እንዲሁም የፍትሕ እና የድጋፍ ሰጪ ተቋማት አገልግሎቶች ተደራሽ መሆናቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት።

ሆኖም በክትትሉ የወንጀል ፍትሕ አገልግሎት እና የድጋፍ ሰጪ ተቋማት ሁለንተናዊ ተደራሽነት ውስን መሆን፤ ተጎጂዎችን ለሁለተኛ ደረጃ ጥቃት የሚያጋልጡ አሠራሮች መኖር፤ በሴቶች እና በሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን አስመልክቶ ከመደበኛው የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ውጪ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ደንቦች አለመኖር፤ ለጥቃት ተጎጂዎች የሚሰጥ የደኅንነት ጥበቃ አለመሟላት እና የተቀናጀ የአንድ ማእከል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በተቀመጠላቸው የአሠራር ሥርዓት ማኑዋል መሠረት አለመሥራት የጥቃት ተጎጂ ሴቶች እና ሕፃናት ሰብአዊ መብቶች አያያዝ የጥሰት ምክንያቶች ናቸው።

በመሆኑም መንግሥት ለመብት ጥሰቶቹ ምክንያት የሆኑትን የሕግ እና የአሠራር ክፍተቶች በማጤን በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ የጥቃት ተጎጂ የሆኑ ሴቶች እና ሕፃናት ሰብአዊ መብቶች አያያዝን ለማሻሻል አስፈላጊ እርምጃዎችን መውሰድ ይገባዋል። በተጨማሪም በተቀናጀ የአንድ ማእከል መስጫ ተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶች ደረጃቸውን የጠበቁ፤ የተደራጁ እንዲሁም ወጥ የሆነ ሥርዓትን የተከተሉ እንዲሆኑ ለማስቻል የሚረዱ እርምጃዎች መንግሥት በአፋጣኝ መውሰድ ይገባዋል።

### 4.2 ምክረ-ሐሳቦች

በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት ውስጥ የጥቃት ተጎጂ የሆኑ ሴቶችና ሕፃናት መብቶች አያያዝ የተሻለ ለማድረግ የሚከተሉት የመፍትሔ ሐሳቦች ታሳቢ ሊሆኑ ይገባል።

- በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሰነዶች ዕውቅና የተሰጣቸው የጥቃት ተጎጂዎች መብቶች በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲም ዕውቅና የተሰጣቸው በመሆኑ የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናትን የተለየ አያያዝ የሚመለከት ግልጽ የሕግ ማዕቀፍ እንዲደነገግና፤ የፍትሕ ሚኒስቴርም የሕጎቹን ተግባራዊነት እንዲያስተባብር፣ እንዲከታተል እና እንዲያረጋግጥ፤
- የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር፣ የፍትሕ ሚኒስቴር፣ የክልል ፍትሕ ቢሮዎች፣ የፌዴራል እና የክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች፣ የፌዴራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች ለፍትሕ እና የድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች የጥቃት ተጎጂ ሴቶችን እና ሕፃናትን ለማስተናገድ

የሚያስችል አስፈላጊውን ስልጠና የወሰዱ ሰራተኞችን እንዲያዘጋጁ እና ለዚሁ አገልግሎት ብቁ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሥርዓት እንዲዘረጉ፤

- የፍትሕ ሚኒስቴር፣ የክልል ፍትሕ ቢሮዎች፣ የፌዴራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች እንዲሁም የፌዴራል እና የክልል ፖሊስ ኮሚሽኖች በአግባቡ በመቀናጀት የወንጀል ምርመራ የሚጠናቀቅበትን እና በጉዳዩ ላይ ክስ ማቅረብ የሚቻልበትን የጊዜ ገደብ በተመለከተ አስፈላጊውን መመሪያዎችን እንዲያወጡ እና ፍትሕ ሚኒስቴር ተግባራዊነቱን እንዲከታተል፤
- የፌዴራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች በወንጀል ድርጊት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ለደረሰው ጉዳት በፍርድ ቤት ወይም በሌሎች አማራጭ ዘዴዎች የካሳ ጥያቄ በማቅረብ ተገቢውን ካሳ በአፋጣኝ እንዲያገኙ ማድረግ የሚያስችሉ አመቺ የአሠራር ሥርዓቶችን እንዲዘረጉ፤
- ፍትሕ ሚኒስቴር እና የፌዴራል ፖሊስ፣ ከክልል ፍትሕ ቢሮዎች እና ከሌሎች ባለ ድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የጥቃት ተጎጂ ሴቶችና ሕፃናት በወንጀል ፍትሕ አስተዳዳር በሚያልፉበት ጊዜ አስፈላጊ መረጃዎችን የሚሰጡ የመረጃ አገልግሎት ማእከላትን እንዲያቋቁሙ፤
- የፍትሕ ሚኒስቴር፣ የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የጤና ሚኒስቴር፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ አዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን እንዲሁም በክልል የሚገኙ አቻ ተቋማት የተቀናጀ የአንድ ማዕከላትን ኢኮኖሚያዊ ተደራሽነት ችግር ለመቅረፍ በቅርበት በሚገኙ ጤና ጣቢያዎች የሕግ እና የሥነ ልቦና ባለሙያዎችን ጨምሮ አስፈላጊውን የሰው ኃይል በመመደብ የአንድ ማእከል አገልግሎት እንዲሰጡ እንዲያደርጉ፤
- በተቀናጀ የአንድ ማእከል አገልግሎት የአሠራር ማኑዋል መሠረት የፍትሕ ሚኒስቴር እና የክልል ፍትሕ ቢሮዎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በተቀናጀ የአንድ ማዕከል ተቋማት የዐቃቤ ሕግ እና ፖሊስ የሥራ ክፍሎች በአካል አገልግሎት እንዲጀምሩ እንዲያደርጉ፤
- የጥቃት ተጎጂ ለሆኑ ሴቶችና ሕፃናት አስፈላጊ የሆኑ የመጠለያ፣ የማገገሚያ እንደ ሕክምና እና የሥነ ልቦና አገልግሎቶች ያሉ መፍትሔዎች በሕግ ዕውቅና እንዲሰጥ፤
- በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረት የየፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንቶች የጾታ ጥቃት የተፈጸመባቸው ሴቶች፣ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያንን አስመልክቶ በፍርድ ቤቶች የሚከፈቱ መዝገቦች በተፋጠነ ፍትሕ አገልግሎት እልባት እንዲያገኙ እና የሕግ ባለሙያ ድጋፍ እንዲሰጣቸው ለማድረግ የሚያግዙ ዝርዝር መመሪያዎችን እንዲያወጡና እንዲያስፈጽሙ፤
- የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከክልል የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ጋር በመተባበር በፌዴራል እና በክልሎች የማገገሚያ አገልግሎቶችን የሚሰጡ የመጠለያ ተቋማትን እንዲያቋቁሙ እና እንዲያስፋፉ፤

- ሕግ አውጪው የጥቃት ተጎጂዎች ሴቶች እና ሕፃናት ደኅንነት ለመጠበቅ የሚያስችል ሕግ እንዲያወጣ እንዲሁም የፍትሕ ሚኒስቴር ሕጉን ማስፈጸም የሚያስችል የአሠራር መዋቅር እንዲዘረጋ፡፡